# ማሰቃየት ፍፁም መከልከሉ፤ ተጨባጭ ተስፋ ወይስ ላም አለኝ በሰማይ?

**በድሉ ታደሰ♣**

**Abstract**

*The absolute prohibition of torture and other ill-treatment has been a subject of vehement debate over the years. Although torture has long been absolutely prohibited under international, regional and national human rights laws, systematic and widespread practice of torture persists all over the world. Against this backdrop, this article aims to explore the conundrum underlying such vile practice perpetrated under the guise of national security and counter-terrorism. It is written in the Amharic language under the title "The Absolute Prohibition of Torture: Realistic Expectation or Pie in the Sky?". Drawing on doctrinal analysis, it discusses the legal basis of the absolute prohibition of torture, the tension between this prohibition and the indefensible practice, and the criteria distinguishing torture from ill-treatment. It exemplifies the jurisprudence of the UN and regional human rights systems advocating for the absolute prohibition of torture as an inviolable norm. It puts forward several cogent arguments for the absolute prohibition of torture, an act which is abhorrent to every right-minded person. Consequently, the article calls for the transition from impunity to accountability and emphasises the need to uphold the rule of law.*

**Keywords**: Torture, Ill-Treatment, Cruel, Absolute Prohibition, Case Law

DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.8

This article is licensed under a Creative Commons Attribution (CC BY)

**Accepted: 10 April 2025** **Published: 20 June 2025**

**Recommended Citation: በድሉ ታደሰ**, '**ማሰቃየት ፍፁም መከልከሉ፤ ተጨባጭ ተስፋ ወይስ ላም አለኝ በሰማይ?**', *Hawassa University Journal of Law*, Vol. 9. (2025), PP. 213-254. DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.8

♣ LLB, LLM, Senior Human Rights Officer in Ethiopian Human Rights Commission (EHRC), Monitoring and Investigation Department, Addis Ababa, Ethiopia, Email: meaza.ayalew2023@gmail.com

 DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.8

## 1. መግቢያ

ማሰቃየትና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ፍፁም መከልከሉ በሁሉም ሀገራት ላይ አስገዳጅ መርሆ (*jus cogens*) ሆኖ[1] በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተቀባይነት ካገኘ (እ.ኤ.አ. 1987) ሠላሳ ሰባት ዓመታት አልፈዋል። ክልከላው ማሰቃየትና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣትን ለማስቀረት በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስምምነት ተደንግጓል። ይህ ስምምነት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከዚህ በኋላ 'የፀረ ማሰቃየት ስምምነት' እየተባለ የሚጠቀስ ይሆናል። ይህ በሕግ አስገዳጅነት ያለው ስምምነት በሥራ ላይ የዋለው ሰኔ 19 ቀን 1979 ዓ.ም. ነበር። ይህ ቀን ለስምምነቱ መታወሻነት እንዲሁም የማሰቃየት ተግባር ፈጽሞ ስለመከልከሉ ማስታወስ ይቻል ዘንድ የድርጊቱ ሰለባ የሆኑ ተጎጂዎችን የመደገፍ ዓለም አቀፍ ቀን ተብሎ ተከብሮ ይውላል።

የጽሑፉ ዓላማ የአንድ ሀገር ደኅንነትን ለመጠበቅ እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል የማሰቃየት ተግባርን መጠቀም ተገቢ ነው የሚል የተለመደ ግን የተሳሳተ አረዳድን ማብራራት ሲሆን ጽሑፉ በተለይ በሀገሪቱ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ለሚሳተፉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጊዜ ቀጠሮ ችሎትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ለሁሉም የሕግ አስከባሪዎችና ከሕግ ውጭ ትዕዛዝ ለሚሰጧቸው የመንግሥት ባለሥልጣናት እንዲሁም ለጋዜጠኞች ጠቃሚ ግንዛቤ ያስጨብጣል። ጽሑፉ በመጀመሪያ ማሰቃየትና ሌሎች የኢሰብዓዊ አያያዝና ቅጣት ዓይነቶች በሕግ ፍፁም መከልከላቸው ፈጽሞ ተገቢነት ከሌለው (ወይም ምንም ምክንያት ሊቀርብበት ከማይችለው) አሠራር ጋር ያለውን አጣብቂኝ ያብራራል። የክልከላው ሕጋዊ መሠረት የሆኑ አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ፣ አኅጉራዊ እና ሀገራዊ የሰብዓዊ መብት ሕግጋት ድንጋጌዎችን በአጭሩ ይዳስሳል። ማሰቃየትን

---

[1] Manfred Nowak, 'Challenges to the Absolute Nature of the Prohibition of Torture and Ill-Treatment' Netherlands Quarterly of Human Rights, Vol. 23, No. 4, 2005, p. 674.; CAT, 'General Comment No. 2' in 'Note by the Secretariat, Compilation of General Comments and General Recommendations Adopted by Human Rights Treaty Bodies' (24 January 2008) UN Doc CAT/C/GC/2, p. 1.

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

ከሌሎች የኢሰብዓዊ አያያዝና ቅጣት ዓይነቶች ለመለየት የሚያገለግለው በእያንዳንዱ ጉዳይ ይዘት ላይ የተመረኮዘውን መስፈርት ይገልጻል፡፡ ከማሰቃየትና ሌሎች የኢሰብዓዊ አያያዝና ቅጣት ዓይነቶች ጋር በተያያዘ የተባበሩት መንግሥታት የፀረ ማሰቃየት ኮሚቴ (*CAT*)፣ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ (*HRC*) እና ከሦስት አኅጉራዊ የሰብዓዊ መብት ሥርዓቶች የተገኙ የተመረጡ የሚደነቁ ውሳኔዎችን በጊዜ ቅደም ተከተላቸው ያቀርባል፡፡ በሰው ልጆች ላይ ከሚፈጸሙ እጅግ አሰቃቂ ድርጊቶች መካከል አንዱ የሆነው ማሰቃየት በፍፁም መከልከሉን የሚያስረዱ ጠንካራ የመከራከሪያ ነጥቦችን በአመክንዮ አስደግፎ ያቀርባል፡፡ በመጨረሻም የማሰቃየት ተግባርን ማስወገድ እንዲሁም በሕግ ተጠያቂነት ካለመኖር ወደ ተጠያቂነትንና የሕግ የበላይነትን በተግባር ማረጋገጥ መሸጋገር አስፈላጊ መሆኑን አጉልቶ ያሳያል፡፡

ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለው ከሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግለው ዘዴ የሆነው የሰነድ ትንተና ሲሆን ሁሉም ጥቅም ላይ የዋሉ ተዓማኒነት ያላቸው የሕትመት ውጤቶች እና ከነፃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች በዋቢነት በሚገባ ተጠቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም ፀሐፊው በዘርፉ ያካበተውን ሰፊ ልምዱን ተጠቅሟል፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ፀሐፊው የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት የፍርድ ውሳኔ ሕግን (*case law*) እንደማመሳከሪያ ነጥብ ተጠቅሟል፡፡ ምክንያቱም በርካታ የዓለም አቀፍ ሕግ ምሁራን ፍርድ ቤቱን በዓለም ላይ እጅግ በጣም አንጋፋ እና ስኬታማው አኅጉር አቀፍ የሰብዓዊ መብት ፍርድ ቤት አድርገው ይመለከቱታል፡፡[2]

---

[2] Michael Goldhaber, *A People's History of the European Court of Human Rights*, (Rutgers University Press, 2008) p. 2; Andreas von Staden, *Strategies of Compliance with the European Court of Human Rights: Rational Choice Within Normative Constraints*, (University of Pennsylvania Press 2018); Tomáš Ľalík, *Understanding the Binding Effect of the Case-Law of the ECtHR in Domestic Legal Order*, <https://papers.ssrn.com/sol3/papers.cfm?abstract_id=1951830> accessed on August 28, 2024; Laurence R. Helfer, *Redesigning the European Court of Human Rights: Embeddedness as a Deep Structural Principle of the European Human Rights Regime* <https://academic.oup.com/ejil/article/19/1/125/430843> accessed on August 28, 2024; Frank Emmert and Chandler Carney, *The European Union Charter of Fundamental Rights vs. The Council of Europe Convention on Human Rights and Fundamental Freedoms - A Comparison* <https://ir.lawnet.fordham.edu/ilj/vol40/iss4/1/> accessed on August 28, 2024.

ፍርድ ቤቱ የሚጠቀመው ዋነኛ የሕግ አተረጓጎም ዘዴ 'የሕያው ሰነድ ቀኖና' ('*living instrument doctrine*') በመሆኑ የስምምነቱ ድንጋጌዎች ከወቅታዊ ሁኔታዎች አንጻር ይተረጎማሉ::[3] ሆኖም ፍርድ ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በአባል ሀገራት ካለመተግበር ጋር በተያያዘ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል::[4]

## 2. ማሰቃየት ፍፁም ስለመከልከሉ፤ የማሰቃየት ትርጓሜ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች

የፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 1(1) 'ማሰቃየት' ('*Torture*') ማለት፦

> *ከራሱ ወይም ከሦስተኛ ወገን መረጃ ለማግኘት ወይም የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም እንዲናዘዝ ታስቦ አንድ ሰው ላይ ሆን ተብሎ የሚፈጸም ከመጠን ያለፈ አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ሕመምና ስቃይ እንዲሁም ሰውየው ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገን በፈጸመው ወይም ፈጽሟል ተብሎ በተጠረጠረበት ድርጊት ለመቅጣት፣ ለማስፈራራት፣ ለማስገደድ ወይም በማናቸውም ዓይነት ልዩነት ላይ ለተመሰረተ ማንኛውም ምክንያት በመንግሥት ባለሥልጣን ወይም በሌላ የመንግሥት ሥልጣን ይዞ በሚሰራ ሰው አነሳሽነት፣ ፈቃድ ወይም አውቆ ሳለ ባለመቃወም የሚፈጸም ድርጊት ነው'* ብሎ ትርጉም ሰጥቶታል፤ ይህም ከሕጋዊ ቅጣቶች ውስጠ-ባህሪይ የሚመነጭ ወይም በአጋጣሚ የሚከሰት ሕመምን ወይም ስቃይን አይጨምርም::[5]

---

[3] George Letsas, 'Chapter 4 - The ECHR as a living instrument: its meaning and legitimacy' in Andreas Føllesdal, Birgit Peters and Geir Ulfstein (eds.), *Constituting Europe: The European Court of Human Rights in a National, European and Global Context* (Cambridge University Press, 2013).

[4] Dia Anagnostou (ed.), *The European Court of Human Rights Implementing Strasbourg's Judgments on Domestic Policy* (Edinburgh University Press, 2013); Kanstantsin Dzehtsiarou and Vassilis P. Tzevelekos, *The Conscience of Europe that Landed in Strasbourg: A Circle of Life of the European Court of Human Rights* <https://brill.com/view/journals/eclr/1/1/article-p1_1.xml> accessed on August 27, 2024.

[5] በተጨማሪም ኢሰመኮ፣ *የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ*፣ ጥር 2004 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 107 ይመለከቷል።

በዚህ ትርጓሜ መሠረት አንድ ድርጊትን ማሰቃየት ነው ለማለት ቢያንስ አራት መሠረታዊ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡ እነዚህም ድርጊቱ ከባድ አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ሕመምና ስቃይ የሚያካትት መሆኑ፣ ሆን ተብሎ የተፈጸመ መሆኑ፣ የተፈጸመው ለተጠቀሰው ዓላማ መሆኑ እና የመንግሥት ባለሥልጣናት ተሳትፎ መኖር ናቸው፡፡ ይህን የማሰቃየት ደረጃ የማያሟላ አድራጎት ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በእርግጥ ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 5 እና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን (ICCPR) አንቀጽ 7 ማንም ሰው ከማሰቃየትና ሌላ ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት እንዳለው ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ የመግለጫው ድንጋጌ የተጠቀሰውን አድራጎት ለመከልከል ጠቅላላ አነጋገር ወይም ግልጽ ያልሆኑ ቃላትን ከመጠቀሙም ባሻገር ማሰቃየትና ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣትን በሚከለክለው መለኪያ በሀገራት ላይ የሕግ አስገዳጅነት እንደሚኖረው በግልጽ አላስቀመጠም፤ የቃል ኪዳኑ ድንጋጌ ደግሞ በተለይ የሕክምና ወይም ሳይንሳዊ ሙከራን የሚመለከት ተጨማሪ ዐረፍተ ነገር በማከል የመግለጫውን ድንጋጌ ቋንቋ ከመድገሙ በቀር የተፈጻሚነት ወሰኑን አይገልጽም፡፡[6] እንዲሁም ይኸው የቃል ኪዳኑ ድንጋጌ የድርጊቱ ፈጻሚ 'በመንግሥት ባለሥልጣን ወይም በሌላ የመንግሥት ሥልጣን ይዞ በሚሰራ ሰው' መሆን እንዳለበት በፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገውን መስፈርት አላካተተም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጽሑፎች ሀገራት

[6] Christof Heyns, Carmen Rueda and Daniel du Plessis, 'Chapter 6. Torture and ill treatment: the United Nations Human Rights Committee' in Malcolm D. Evans and Jens Modvig (eds.), *Research Handbook on Torture: Legal and Medical Perspectives on Prohibition and Prevention* (Edward Elgar Publishing Limited, 2020).

መግለጫውን ያለማቋረጥ ከሃምሳ ዓመታት በላይ ምክንያት አድርገው በማቅረባቸው የልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግ አካል በመሆን አስገዳጅ ሆኗል በማለት ይከራከራሉ።[7]

የፀረ ማሰቃየት ስምምነትን ያጸደቁ ሀገራት ላይ በርካታ ግዴታዎች ተጥሎባቸዋል። ከእነዚህም መካከል በአንቀጽ 4 እና አንቀጽ 12 ላይ እንደተገለጸው የሁሉም ሀገራት መሠረታዊው የሕግ ግዴታ ማንኛውንም የማሰቃየት ተግባር የሚያስቀጣ ወንጀል ማድረግና ተፈጽመዋል በሚል የሚቀርቡ ውንጀላዎችን መመርመር ነው። ነገር ግን በቅርቡ ለተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት በቀረበው የማሰቃየት ጉዳይ የሚመለከተው ልዩ ራፖርተር ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው በሀገራት ዘንድ የማሰቃየት ወንጀል ምርመራና ክስን በተመለከተ ተግዳሮቶችና መልካም ልምዶች እንዳሉ እንዲሁም ማሰቃየት ተፈጽሟል በሚል የሚቀርቡ ውንጀላዎች (*allegations*) ላይ የተሟላና ፈጣን ምርመራ ለማካሄድ የሚከለክሉ ተቋማዊ፣ የሕግ፣ ፖለቲካዊና ተግባራዊ መሰናክሎች መኖራቸው ተገልጿል።[8]

በአኅጉር ደረጃ ደግሞ ክልከላው በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 5፣ በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3፣ በአውሮፓ ኅብረት የመሠረታዊ መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4፣ በአሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 5(2)፣ ማሰቃየትን ለመከላከል እና ለመቅጣት የወጣው የኢንተር አሜሪካ ስምምነት አንቀጽ 2(1)፣ በደቡብ ምሥራቅ እስያ መንግሥታት ማኅበር የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 14፣ በእስያ የሰብዓዊ መብቶች ቻርተር አንቀጽ 3.3፣ 3.5፣ 14.2፣ በአረብ የሰብዓዊ መብቶች ቻርተር አንቀጽ 8(1) እና በካይሮ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 20 ውስጥ ተካትቷል። በእርግጥ እያንዳንዱ አኅጉር

---

[7] Australian Human Rights Commission, *What is the Universal Declaration of Human Rights?* <https://humanrights.gov.au/our-work/commission-general/projects/what-universal-declaration-human-rights> accessed 11 February 2025.

[8] UN Special Rapporteur on Torture and Other Cruel, Inhuman or Degrading Treatment or Punishment (Alice Jill Edwards), 'Report of the Special Rapporteur on torture and other cruel, inhuman or degrading treatment or punishment: Good practices in national criminalization, investigation, prosecution and sentencing for offences of torture' (2023) A/HRC/52/30.

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሥርዓት የራሱ የሆኑ ልዩ ባህሪያት እንዳሉት ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ከአብዛኛዎቹ ሰብዓዊ መብቶች በተለየ መልኩ ከማሰቃየት ወይም ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት ከጥቂት ፍፁም መብቶች መካከል አንዱ ነው፡፡[9] ይህ ማለት ሰዎችን ለማሰቃየት ምንም እንደመከላከያ ምክንያት አድርጎ ማቅረብ አይቻልም፡፡ ማሰቃየትና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መከልከሉ ፍፁምና ምንም ልዩ ሁኔታ (*exception*) የሌለው ነው፡፡ ፍፁም መብቶች በማንኛውም ምክንያት ሊገደቡ እና በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ውስጥም ቢሆን ሊታገዱ አይችሉም፡፡[10]

ይሁን እንጂ የማሰቃየት መከልከል ፍፁምነት እስካሁን ድረስ በፖለቲከኞች፣ በሕግ አስከባሪዎች እና በምሁራንም ዘንድ ጥያቄ ውስጥ ገብቷል፡፡ ለአብነት ለመጥቀስ ያህል አንዳንድ የሰብዓዊ መብት ምሁራን በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ውስጥ የተደነገገው ማሰቃየትና ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መከልከሉ ፍፁም ነው መባሉ ችግር ያለበት ወይም አጠያያቂ ነው ሲሉ ይተቻሉ፡፡[11] ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ያቀርባሉ፤ በመጀመሪያ ፍፁምነት የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ግልጽ፣ ተፈጥሯዊ፣ የተረጋገጠ

---

[9] የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን [በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ ቁጥር 2200 A (XXI) እ.ኤ.አ. ታኅሣሥ 16 ቀን 1966 ዓ.ም. የጸደቀና እ.ኤ.አ. መጋቢት 23 ቀን 1976 ዓ.ም. ሥራ ላይ የዋለ] አንቀጽ 7፣ አንቀጽ 8(1) እና 8(2)፣ አንቀጽ 11፣ አንቀጽ 15 እና አንቀጽ 16 ይመለከቷል፤ እነዚህም ከማሰቃትና ሌላ ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ ነፃነት፤ በባርነትና በግዴታ አገልጋይነት ያለመያዝ ነፃነት፣ የውል ግዴታን ባለማሟላት ምክንያት ያለመታሰር ነፃነት፤ የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ እንዳይሰራ መከልከሉ፤ በሕግ ፊት ዕውቅና የማግኘት መብት ናቸው።

[10] የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 7; Nowak (n 1) 688; CAT (n 1) 2; The UN Committee on International Covenant on Civil and Political Rights, 'General Comment No. 20' in 'Note by the Secretariat, Compilation of General Comments and General Recommendations Adopted by Human Rights Treaty Bodies' (10 March 1992).

[11] Steven Greer, Is the Prohibition against Torture, Cruel, Inhuman and Degrading Treatment Really 'Absolute' in International Human Rights Law? Human Rights Law Review, Vol. 15, No. 1, 2015, p. 101; Mirko Bagaric and Julie Clarke, 'Not Enough Official Torture in the World? The Circumstances in which Torture is Morally Justifiable', University of San Francisco Law Review, Vol. 39, No. 3, 2005, p. 581.

ወይም አስፈላጊ ባህሪይ ስላልሆነ ይህ አቋም ከተፈጥሮአዊ የአስገዳጅነት/አስፈላጊነት ሕግ ይልቅ ውጫዊ ባህሪይ የመስጠት ጉዳይ ነው። ሌሎች ፍፁም አይደለም የሚሉ አተረጓጎሞች እውነት ሊሆኑ ወይም ላይሆኑ የሚችሉ እና በአንዳንድ ዝነኛ ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች ላይ የሰፈሩትን ተመሳሳይ ክልከላዎች በግልጽ ያረጋግጣሉ። 'ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ' የሚለው ቃል በተለምዶ ማሰቃየትን በሚከለክሉ ተመሳሳይ አንቀጾች ውስጥ የተካተተ በመሆኑ እነዚህ በጣም የተለያዩ ጎጂ ድርጊቶች የግድ ተመሳሳይ ቦታ ሊኖራቸው ይገባል ወደሚል ድምዳሜ አያደርስም። በተጨማሪም ክልከላው በመርህ ደረጃ ፍፁም ነገር ግን በተፈጻሚነቱ አንጻራዊ ነው መባሉ አሳማኝ አይደለም። በመጨረሻም በሞራል ወይም በሕግም ሆነ በአመክንዮ ማንኛውም 'ፍፁም' መብት ካሉት ሁለት ተፎካካሪ አጋጣሚዎች ለእያንዳንዱ ትርጉም ባለው መልኩ እኩል 'ፍፁም' መሆኑ የማይቻል ነው። በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ውስጥ የተደነገገው ማሰቃየት እና ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መከልከሉ በጥብቅ ፍፁም ሳይሆን ይልቁንም 'ለፍፁም ትንሽ የቀረው' ብቻ ሊሆን ይችላል። በጣም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር በሁሉም ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል በማለት ይከራከራሉ።

በእርግጥ አንድ ታዋቂ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግ ምሁር በጽሑፋቸው ውስጥ ማሰቃየት መከልከሉን በተመለከተ አራት የተለያዩ ተግዳሮቶች እንዳሉ እና ለእነዚህ ተግዳሮቶች የሚሰጡ (እውነት ሊሆኑ ወይም ላይሆኑ የሚችሉ) የሕግ ምላሾችን ያብራራሉ። እነዚህም 1ኛ) የጊዜ ቦምብ ክስተት (ማለትም በቶሎ መፍትሔ ካልተበጀለት ውሎ አድሮ አደገኛ ሊሆን የሚችል ችግር ያለበትን ሁኔታ ይገልጻል) ('*ticking time bomb scenario*')፣ 2ኛ) በአንድ በኩል ማሰቃየት መከልከሉ እንደ ፍፁም መብት እና በሌላ በኩል ደግሞ ጭካኔ የተሞላበት ኢሰብዓዊና ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መከልከሉ እንደ አንጻራዊ መብት መካከል ያለው ልዩነት፣ 3ኛ) በፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 1 ላይ የሰፈረው ሕጋዊ የተፈቀዱ ሁኔታዎችን የያዘው ድንጋጌ፣ እና 4ኛ) ከማሰቃየት መከልከል የመነጨውን

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

ስደተኞችንና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ማሳድደ ወይም ስቃይ ይደርስብናል ብለው ወደሚሰጉበት ሀገር አስገድዶ ያለመመለስ መርሆ (*principle of non-refoulement*) ፍፁማዊ ተፈጥሮን ለመጣስ ዲፕሎማሲያዊ ማረጋገጫዎችን (*diplomatic assurances*) እንደ ዘዴ መጠቀም ናቸው::[12]

## 2.1 ኢሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ምንድን ነው?

በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት የፍርድ ውሳኔ ሕግ መሠረት አንድ አያያዝ 'ኢሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ' ('*inhuman or degrading*') ተብሎ እንዲወሰድ፡-

- በአንድ ግለሰብ ላይ የተፈጸመው ስቃይ እና ውርደት በሕግ የተደነገገ ተገቢ የሆነው አያያዝ ወይም ቅጣት ያስከተለው የማይቀር ስቃይ ወይም ውርደት አካል ከሆነው መጠን/ወሰን በላይ/ያለፈ መሆን አለበት::
- በግለሰቡ ላይ ተፈጽሟል የተባለው ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት (*ill-treatment*) መጠኑ ዝቅተኛ ከሆነው ከባድነት/ክብደት ላይ መድረስ አለበት፤ ከባድነቱን መወሰንም ከሌሎች ነገሮች መካከል በተለይ ከአያያዙ ቆይታ፣ በግለሰቡ ላይ ከደረሰው አካላዊ እና/ወይም አዕምሮአዊ ተጽዕኖ እና ከግለሰቡ ፆታ፣ ዕድሜና የጤና ሁኔታ ጋር በተያያዙ የጉዳዩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው::

በተለይም ነፃነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች ጠባያቸው በጥብቅ አስፈላጊ ያላደረገውን አካላዊ ኃይል ለመጠቀም የወሰዱት ማናቸውም አማራጭ እርምጃ ሰብዓዊ ክብርን ያሳንሳል፤ እናም በመርህ ደረጃ የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 ድንጋጌን ይጥሳል::[13]

ፍርድ ቤቱ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት አንድ ቅጣት ወይም አያያዝ 'ክብርን የሚያዋርድ' መሆኑን ሲገመግም የሚከተሉትን ይመለከታል፡-

---

[12] Nowak (n 1) 675.
[13] *Ribitsch v Austria* App no 18896/91 (ECtHR, 4 December 1995) para. 38.

- የአያያዙ ዓላማ ግለሰቡን ለማዋረድ እና ክብሩን ዝቅ ለማድረግ እንደሆነ[14] እና እንደአማራጭ፣
- አያያዙ የሚያስከትለውን ውጤት በተመለከተ በአንቀጽ 3(10) ላይ ከተደነገገው ጋር በማይጣጣም መልኩ በግለሰቡ ስብዕና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር/የሚጉዳ እንደሆነ[15]፣
- እንዲሁም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ተጎጂውን ሊያዋርድ ወይም ክብሩን ዝቅ ሊያደርግ እና ምናልባትም የተጎጂውን አካላዊ ወይም ሞራላዊ የመቋቋም ኃይል መስበር የሚችል ለምሳሌ ፍርሃት፣ ጭንቀት እና የበታችነት ስሜትን የሚቀሰቅስ አያያዝን የሚያካትት ተደርጎ ይታያል፡፡[16] ለምሳሌ አንድ ሐኪም አደጋ የደቀነ መሆኑን ያመላከተ ማንኛውም ማስረጃ ሳይኖር በቤተሰቡና በጎረቤቶቹ ፊት ለፊት እጁን በካቴና ማሰር እንዲህ ዓይነት ስሜት እንደቀሰቀሰ እና ስለዚህ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ተደርጎ ተወስዷል፡፡[17]

በፀረ ማሰቃየት ስምምነት ላይ የሰፈረውን ትርጓሜ ፍርድ ቤቶች እንደተረጎሙት፤ 'ማሰቃየት' ('torture')፦

- ከባድ የአካል ወይም የአዕምሮ ሕመም ወይም ስቃይ ያስከትላል፡፡
- ሆን ተብሎ የሚፈፀም ነው፡፡
- ለተወሰነ ዓላማ (ማለትም እንደ የእምነት ቃል ያለ መረጃ ለማግኘት፣ ለቅጣት፣ ለማስፈራራት፣ ወይም ለሌሎች አድሎአዊ ምክንያቶች) የሚፈፀም ነው፡፡
- በአንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ቢያንስ ያለተቃውሞ በመቀበሉ (acquiescence) የተፈጸመ ነው፡፡ በቀጥታ እርምጃ በመውሰድ ወይም

[14] *Campbell and Cosans v United Kingdo*m App no 7511/76 (ECtHR, 25 February 198) para. 30.
[15] ዝኒ ከማሁ
[16] *Keenan v United Kingdom* App no 27229/95 (ECtHR, 3 April 2001) para. 109.
[17] *Erdogan Yagiz v Turkey* App no 27473/02 (ECtHR, 6 March 2007).

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

በሌሎች የሚፈጸም ማሰቃየትን ለመከላከል ተገቢውን እርምጃ ባለመውሰድ የሆነ ዓይነት የመንግሥት ባለሥልጣናት ተሳትፎ መኖር አለበት፡፡[18]

### 2.2 ማሰቃየት ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ ከሆነ አያያዝ እንዴት ይለያል?

በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን፣ በፀረ ማሰቃየት ስምምነት እንዲሁም በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር ላይ በማሰቃየት እና ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መካከል ያለው ትክክለኛ ልዩነት ግልጽ አይደለም፡፡[19] በሁሉም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ላይ ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣትን በተመለከተ ምንም ዓይነት ትርጓሜ አልተሰጠም፡፡

በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት የፍርድ ውሳኔ ሕግ መሠረት አንድ ድርጊት ማሰቃየት ወይም ኢሰብዓዊ የሆነ/ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ መሆኑ በሚወሰንበት ጊዜ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሦስት ዋና ዋና ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህም፦

(i) *ድርጊቱ ሆን ተብሎ የተፈጸመ መሆኑ (ድርጊቱን የመፈጸም አሳብ መኖሩ)፤* አንድ ሰው ከድርጊቱ በስተጀርባ ያለውን ዓላማ ማየትና መመዘን አለበት፡፡

---

[18] Manfred Nowak, Moritz Birk and Giuliana Monina (eds.), *The United Nations Convention Against Torture and its Optional Protocol: A Commentary* (Oxford University Press, 2019); The United Nations Voluntary Fund for Victims of Torture, *Interpretation of Torture in the light of the Practice and Jurisprudence of International Bodies* <https://www.ohchr.org/sites/default/files/Documents/Issues/Torture/UNVFVT/Interpretation_torture_2011_EN.pdf> accessed on August 1, 2024; Nigel S. Rodley, 'The Definition(s) of Torture in International Law' Current Legal Problems (Oxford University Press), Vol. 55, No. 1, 2002, p. 467.; Gerrit Zach, 'Article 1 Definition of Torture' in Manfred Nowak et. al. (eds.), *The United Nations Convention Against Torture and its Optional Protocol: A Commentary* (Oxford University Press, 2019).

[19] United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC), *Module 9: Prohibition against Torture and other Cruel, Inhuman and Degrading Treatment* <https://www.unodc.org/e4j/zh/terrorism/module-9/key-issues/regional-human-rights-instruments.html> accessed on August 2, 2024; Manfred Nowak, 'Civil and Political Rights, including the Question of Torture and Detention: Report of the Special Rapporteur on torture and other cruel, inhuman or degrading treatment or punishment: Mission to China' (2006) UN Doc E/CN.4/2006/6/Add.6.

ማስቃየት 'በአጋጣሚ' ሊከሰት አይችልም። በአንፃሩ ኢሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ በቸልተኛነት ወይም ድርጊቶች (ለምሳሌ ባለማወቅ አንድ እስረኛን ለሕመም ወይም ለስቃይ መዳረግ እና የመሳሰሉት) በሚያስከትሏቸው ያልታሰቡ ውጤቶች ሊከሰት ይችላል።

(ii) *የሕመሙ ክባድነት*፤ ተፈጽሟል የተባለው ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 ወሰን ውስጥ እንዲወድቅ ከተፈለገ ዝቅተኛው የከባድነት ደረጃ ላይ መድረስ አለበት።[20] የዚህ ዝቅተኛ መለኪያ ግምገማ አንጻራዊ ነው፤ ማለትም በአያያዙ ቆይታ፣ በአካላዊ እና/ወይም አእምሯዊ ውጤቶቹ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ በተጎጂው ፆታ፣ ዕድሜ እና የጤና ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው።[21] ስለሆነም አንድ አያያዝ በአንቀጽ 3 ላይ የተደነገገው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ለመወሰን ሁሉንም የአንድ ጉዳይ ሁኔታዎችን መመልከትን ይጠይቃል። ለማሰቃየት ወይም ጭካኔ ለተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ለሆነ ወይም ክብርን ለሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ሊተገበሩ በሚችሉ የከባድነት ደረጃዎች መካከል ያለውን የልዩነት መስመር መወሰን በጣም አስቸጋሪ ነው። በተጨማሪም የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት 'ሕያው ሰነዶች' በመሆናቸው እየተለወጡ ያሉ የሕዝቡ ግንዛቤና አመለካከቶች መስመሩ በሚሰመርበት ቦታ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ስለዚህ በአስፈላጊነቱ እና በሚፈለገው የከባድነት ደረጃ ላይ ጠንካራ ክርክር መኖሩ አያስገርምም። በአውሮፓ ዐውድ ውስጥ የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት የፍርድ ውሳኔ ሕግ በጣም ጠቃሚ ነው።

(iii) *ዓላማው*፤ ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት በተቃራኒው ማሰቃየት ለአንድ ዓላማ የሚደረግ ድርጊት ነው፤ ይኸውም መረጃ ለማግኘት (ለምሳሌ የእምነት ቃል)፣

---

[20] *Tyrer v United Kingdom* App no 5856/72 (ECtHR, 25 April 1978) para. 30.
[21] *Keenan* (n 16) para. 108; *Campbell* (n 14) para. 30.

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

ለመቅጣት፣ ለማስፈራራት እና አድልዎ/ልዩነት ለማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተገለጸው እንዲህ ያለ ዓላማ ባይኖረውም እንኳ ከመጠን ያለፈ የኃይል አጠቃቀም ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ሊያስከትል ይችላል፡፡

በአንፃሩ ደግሞ አንዳንድ ፀሐፍት የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤትና ብዙ ምሁራን እንደሚከራከሩት ማሰቃየትን ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ለመለየት ወሳኙ መስፈርት የደረሰው ሕመም ወይም ስቃይ ከባድነት ሳይሆን የድርጊቱ ዓላማና የተጎጂውን አቅም ማጣት ነው፤ ልዩነቱ በዋናነት ከግል ነፃነት ጋር የተያያዘ ነው ሲሉ ይከራከራሉ፡፡[22]

## 2.3 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀረ ማሰቃየት ኮሚቴ ተግባራትና የፍርድ ውሳኔ ሕግ

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀረ ማሰቃየት ኮሚቴ በዋናነት በሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት አማካኝነት የፀረ ማሰቃየት ስምምነቱን ባጸደቁ አባል ሀገራት መተግበሩን ይከታተላል፡፡ ኮሚቴው ከማሰቃየት ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ወይም ስምምነቱን ያጸደቁ ሀገራት የበለጠ ትኩረት መስጠት አለባቸው ብሎ ባመነባቸው የዘርፍ ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ አስተያየቶችን ያጸድቃል፡፡ በፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 20 ላይ በተደነገገው መሠረት ኮሚቴው በማንኛውም የፀረ ማሰቃየት ስምምነቱን ባጸደቀች ሀገር ውስጥ ማሰቃየት ስልታዊ በሆነ መልኩ እየተፈፀመ መሆኑን የሚያመለክት አሳማኝ መረጃ ሲቀበል ሚስጥራዊ ምርመራ ሊያካሄድ ይችላል፡፡ እንዲሁም ኮሚቴው በተለያየ ጊዜ ለቀረቡለት አቤቱታዎች የተለያዩ በርካታ ታሪካዊና ወሳኝ ውሳኔዎችን ሰጥቷል፡፡ ከእነዚህ መካከል ኮሚቴው በማሰቃየት ትርጓሜ ውስጥ የተደነገጉትን ድርጊቱን የሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮችን (*elements*) በተመለከተ (በተለይም ከባድ ሕመምና ስቃይ ማድረስ ምን ማለት ስለመሆኑ እና ከባድነት ማሰቃየትን ሌላ ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት

[22] Manfred Nowak & Elizabeth McArthur, 'The distinction between torture and cruel, inhuman or degrading treatment' TORTURE, Vol. 16, No 3, 2006, p. 147.

መለያ መስፈርት ስለመሆኑ) በቡሩንዲ፣ በሩሲያ፣ በካዛኪስታን፣ በስዊዲን እና በአልጄሪያ መንግሥታት ላይ የሰጣቸው የሚከተሉት ውሳኔዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በፓትሪስ ጋሁንጉ እና ቡሩንዲ ጉዳይ ኮሚቴው በአቤቱታ አቅራቢው (ተጎጂ በተባለው) ላይ የተፈጸመበት አያያዝ 'ምናልባት የእምነት ቃል እንዲሰጥ ለማስገደድ ያለመ ነው እና በዚህም ምክንያት በፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 1 መሠረት ማሰቃየት ደርሶበታል በማለት ደምድሟል፡፡[23] እንዲሁም በኢ.ኤን. እና ቡሩንዲ ጉዳይ ሀገሪቱ አቤቱታ አቅራቢው ከተያዘ በኋላ በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የፖሊስ አባላት የፈጸሙት ከባድ ድብደባ እንደ ማሰቃየት ሊመደብ እንደማይችል ተከራከረች፡፡ ምክንያቱም የቡሩንዲ የወንጀል ሕግ መረጃ ለማግኘት ወይም የእምነት ቃል ለማግኘት የማሰቃየት ድርጊቶች መፈፀም እንዳለባቸው ያስገድዳል፡፡ ኮሚቴው ግን ድብደባው የተፈፀመው አቤቱታ አቅራቢው ፈጽሟል ተብሎ በተገመተው ድርጊት ለመቅጣት ሳይሆን አይቀርም ሲል ደምድሟል፡፡[24] በሁለቱም የቡሩንዲ ጉዳዮች ላይ ኮሚቴው በአጠቃላይ አስተያየቱ ላይ የገለጸውን አካሄድ የተከተለ ይመስላል፤ ማለትም የመፈጸም አሳብና ዓላማ የተባሉ ፍሬ ነገሮች ወንጀል አድራጊዎች ያነሳሳቸው ምክንያት ላይ በተጨባጭ መረጃዎች ለማረጋገጥ የማያስችል ምርመራ ማድረግን አያካትትም፤ ነገር ግን በምትኩ በሁኔታዎች ውስጥ ተጨባጭ ውሳኔዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡[25]

ነገር ግን በሰርጌ ኪርሳኖቭ እና የሩሲያ ፌዴሬሽን ጉዳይ ኮሚቴው አቤቱታ አቅራቢው የታሰረበት ሁኔታ… በፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 1(1) ላይ በሰፈረው ትርጉም መሠረት ከባድ ሕመምና ስቃይ ያስከተለ አይመስልም ሲል ደምድሟል፡፡[26] ስለሆነም ኮሚቴው ምንም ዓይነት ማብራሪያ ሳይሰጥ በአንቀጽ 16 መሠረት ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ

---

[23] *Patrice Gahungu v Burundi* (2015) UN Human Rights Committee, paras 7.2, 7.3.
[24] *EN v Burundi* (2015) UN Human Rights Committee, para 4.4.
[25] CAT (n 1), para 9.
[26] *Sergei Kirsanov v Russian Federation* (2014) UN Human Rights Committee, para 11.2.

ሆኖ አግኝቶታል። በኮሚቴው አመለካከት የከባድነት መስፈርት ባለመሟላቱ ምክንያት ከዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰ ይመስላል።

በአሌክሳንደር ጌራሲሞቭ እና ካዛኪስታን ጉዳይ አቤቱታ አቅራቢው እጆቹ ወደኋላው ታስረው በወለሉ ላይ እንዲደፋ ከመገደዱ በፊት በኩላሊቱ ላይ ብዙ ከባድ ድብደባና የወሲባዊ ጥቃት ዛቻ ይደርስበት ነበር። በኋላም አቤቱታ አቅራቢው ራሱን ከመሳቱ በፊት የፕላስቲክ ቦርሳ በጭንቅላቱ ላይ ተጭኖ ከአፍንጫው፣ ከጆሮው እና ፊቱ ላይ ካሉ የቆዳ ጭረቶች ደም እስኪፈስ ድረስ ታፍኗል። ኮሚቴው ይህ አያያዝ እንደ ከባድ ሕመምና ስቃይ ሊገለጽ ይችላል በማለት ግኝቱን በግልጽ አሳይቷል፤ እናም ምንም ተጨማሪ ምክንያት ወይም ትንታኔ አልጨመረም። ኮሚቴው ካዛኪስታንን ለብዙ የፀረ ማሰቃየት ስምምነት ጥሰቶች ተጠያቂ አድርጓታል። የጌራሲሞቭ አያያዝ እስከ ማሰቃየት ድረስ በቂ ክብደት የነበረው በመሆኑ የፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 1 ድንጋጌን በመጣስ የእምነት ቃል ለማግኘት የተደረገ ነበር።[27]

ከዚህም በተጨማሪ ኮሚቴው አስገድዶ መድፈርና ሌሎች ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደ ማሰቃየት እንደሚቆጠሩ በግልጽ ዕውቅና ሰጥቷል። በሲ.ቲ.ና ኬ.ኤም. እና ስዊድን ጉዳይ ኮሚቴው በመንግሥት ባለስልጣናት የተፈጸመውን አስገድዶ መድፈር ማሰቃየት እንደሆነ አመላክቷል፤ በዚህም የተነሳ የተከሰተውን ሕመምና ስቃይ ከባድነት አምኖ ተቀብሏል።[28]

በኤች.ቢ. እና አልጄሪያ ጉዳይ ኮሚቴው አቤቱታ አቅራቢውን በሚስጢር ማሰር፣ ማዋረድ እና ኢሰብዓዊ የእስር ቤት ሁኔታዎች የፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 1 ጥሰት እንደሆነ ወስኗል።[29]

ይሁን እንጂ ከፀረ ማሰቃየት ኮሚቴ ጎን ለጎን የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 7 ላይ በተደነገገው መሠረት ተጨማሪ ተመሳሳይ ውሳኔዎችን እንደሚሰጥ ልብ

[27] *Gerasimov v Kazakhstan* (2012) UN Human Rights Committee, paras 2.3, 12.2.
[28] *CT and KM v Sweden* (2006), UN Human Rights Committee, para 7.5.
[29] *HB v Algeria* (2015) UN Human Rights Committee, para 6.3.

 DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.8

ይሏል:: ለአብነት ያህል ለመጥቀስ በጊሪ እና ኔፓል ጉዳይ የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ በፀረ ማሰቃየት ስምምነት የሰፈረውን የማሰቃየት ትርጓሜ እንደሚከተል ከገለጸ በኋላ አጠቃላይ አቀራረቡ በአንድ በኩል በማሰቃየት እና በሌላ በኩል ደግሞ ሌላ ጭካኔ በተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ በሆነ ወይም ክብርን በሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መካከል ያለው ወሳኝ ልዩነት አግባብነት ያለው ዓላማ መኖር አለመኖር ይሆናል ሲል ተከራክሯል::[30] ሌላው በሜግሪሲ እና ሊቢያ አረብ ጃማሂሪያ ጉዳይ የሰብዓዊ መብት ኮሚቴው ከሦስት ዓመታት በላይ ከሰዎች መገናኘትን በማይፈቅድ ሁኔታ በድብቅ ቦታ የተፈጸመ እስር ማሰቃየት እና ጭካኔ የተሞላበት እና ኢሰብዓዊ አያያዝ መሆኑን አረጋግጧል::[31] ከኮሎምቢያ ጋር በተያያዘ ኮሚቴው የአስገድዶ መሰወር ጉዳዮች ከተመረመሩና የሟቾች አስከሬኖች ከተገኘ በኋላ የማሰቃየት ተግባር መፈጸሙን ግልጽ ግኝቶችን አሳይቷል::[32]

ሁለቱም የፀረ ማሰቃየት ኮሚቴም ሆነ የሰብዓዊ መብት ኮሚቴው በደረሰው ከባድ ሕመምና ስቃይ እና ሌሎች የአንቀጽ 1 ላይ የተካተቱት ሌሎች ፍሬ ነገሮች በመሟላታቸው ምክንያት በተለይም በአንድ ሰው ሕይወት ላይ የሚሰነዘር ዛቻ/ማስፈራሪያ ማሰቃየት እንደሆነ ተገንዝበዋል::[33]

## 2.4 አኅጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽኖችና ፍርድ ቤቶች የተመረጡ ውሳኔዎች እና ብሔራዊ የሕግ ማዕቀፎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ማሰቃየትና ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣትን የተመለከቱ ጥሩ ልምዶች ሊባሉ የሚችሉ አኅጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽኖችና ፍርድ ቤቶች የሰጧቸው የተመረጡ ውሳኔዎች እና የሁለት ሀገራት ብሔራዊ የሕግ ማዕቀፎች በአጭሩ ይቀርባሉ:: እነዚህ ለሕግ ጥናት ጠቀሜታ ባላቸው ታሪካዊ ጉዳዮች ላይ የተሰጡ

---

[30] *Giri v Nepal* (2011) UN Human Rights Committee, para 7.5.
[31] *El-Megreisi v Libyan Arab Jamahiriya* (1991) UN Human Rights Committee.
[32] *Bautista de Arellana v Colombia* (1995) and *Arhuacos v Colombia* (1996) UN Human Rights Committee.
[33] CAT 'Report of The UN Committee against Torture' (1997) UN Doc A/52/44, para 257.

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

ውሳኔዎች በመሆናቸው ጉልህ የሆነ አዲስ የሕግ መርሆ ወይም በሌላ መልኩ ነባሩን የሕግ አተረጓጎም በእጅጉ የሚለውጥ ጽንሰ ሐሳብ ያስተዋውቃሉ፡፡

### 2.5 የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን

የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 5 የተፈጻሚነት ወሰንን በተመለከተ የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ውሳኔ የሰጠባቸው በርካታ አቤቱታዎች አሉ፡፡[34] በተለይም እ.ኤ.አ. በ1998 ዓ.ም. በኢንተርናሽናል ፔንና ሌሎች እና ናይጄሪያ ጉዳይ ላይ አንድ መመሪያ ሰጥቷል፤ ኮሚሽኑ እ.ኤ.አ. በ1993 ከኬን ሳሮ-ዊዋ እስር እና እ.ኤ.አ. በ1994 እና በ1995 በእስር ላይ ሳለ ከተፈጸመበት አያያዝ ጋር በተያያዘ (ከሌሎች ነገሮች መካከል) የአፍሪካ ቻርተር አንቀጽ 5 እና 16 ድንጋጌዎች ተጥሰዋል ሲል ወስኗል፡፡[35] በተለይም አንቀጽ 5 ማሰቃየትን ብቻ ሳይሆን ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝንም ይከለክላል፤ ይህም ከባድ የአካል ወይም የሥነ ልቦና ስቃይ ድርጊቶችን ብቻ ሳይሆን ግለሰቡን የሚያዋርዱ ወይም ከፈቃዱ/ከሕሊናው ውጪ እንዲያደርግ የሚያስገድዱ ድርጊቶችንም ይጨምራል፡፡

ኮሚሽኑ ማሰቃየትና ሌሎች ጥሰቶች ተፈጽመዋል ተብለው በቀረቡለት አቤቱታዎች ላይ በሰጣቸው ውሳኔዎች ካዳበረው የፍርድ ውሳኔ ሕግ በተጨማሪም ማሰቃየትና ሌሎች ጥሰቶች ላይ የቀረቡ አቤቱታዎችን በተመለከተ የአፍሪካ የሰብዓዊና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን 'በአፍሪካ ውስጥ ማሰቃየትን ለመከልከልና ለመከላከል የወጣው ሮበን ደሴት መመሪያ' (*Robben Island Guidelines for the Prohibition and Preventing of Torture in Africa*) የተባለ ሰነድ አዘጋጅቷል፡፡ እ.ኤ.አ. በ2017 የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የማሰቃየትና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ወይም ክብርን የሚያዋርድ ቅጣት ወይም አያያዝ ተጎጂ

---

[34] International PEN and Constitutional Rights Project, Civil Liberties Organisation and Interights (on behalf of Ken Saro-Wiwa Jnr.) v Nigeria 1998 ACHPR 1; Civil Liberties Organisation v Nigeria 1999 ACHPR 5; Achuthan (on behalf of Aleke Banda) and Others v Malawi 1994 ACHPR 10; Commission Nationale des Droits de L'Homme et des Liberté v Chad 1995 ACHPR 12; Huri-Laws (on behalf of the Civil Liberties Organization) v Nigeria 2000 ACHPR 23; Ouko v Kenya 2000 ACHPR 27.

[35] ዝኒ ከማሁ International PEN, para. 79.

የሆኑ ሰዎች ካሳ/መፍትሔ የማግኘት መብትን የተመለከተ በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 5 ላይ አጠቃላይ አስተያየት ቁጥር 4 አውጥቷል። እንደሮበን ደሴት መመሪያ በተመሳሳይ አኳኋን ይህ ሰነድ የወጣው "ማሰቃየትና ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት በአፍሪካ አኅጉር ውስጥ አሁንም አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ቀጥሏል እናም ኮሚሽኑ የማሰቃየትና ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ሰለባ የሆኑ ተጎጂዎች መፍትሔ ለማግኘት የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች ይገነዘባል" ለሚለው እውነታ ምላሽ ነው።[36]

### 2.6 የኢንተር አሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የኢንተር አሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት

ሁለቱም የኢንተር አሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የኢንተር አሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት የማሰቃየት መከልከል ግዙፋዊ ገጽታዎችን በሚወስኑበት ጊዜ ድርጊቶቹ ያስከተሉት ሕመም ወይም ስቃይ የቆየበትን ጊዜ፣ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዙ ወይም ቅጣቱ የተፈጸመበትን ምክንያትና ዘዴ፣ አጠቃላይ ዐውዱን፣ ነፃነትን ማሳጣቱ ዘፈቀዳዊ መሆኑን እና የመሳሰሉ ምክንያቶችን እንዲሁም እንደፆታ፣ ዕድሜ እና ማኅበራዊ አቋም ያሉ የተጎጂዎች ግለሰባዊ ባህሪያትን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ።[37] በተጨማሪም እ.ኤ.አ. በ1996 የኢንተር አሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን አስገድዶ መድፈር እንደማሰቃየት ይቆጠራል ሲል ዕውቅና ሰጥቷል። ይኼ አንድ ዓለም አቀፍ አካል አስገድዶ መድፈር በማሰቃየት ወሰን ውስጥ ወድቆ ያገኘበት የመጀመሪያው አጋጣሚ ነበር።[38]

---

[36] ACommHPR, General Comment No. 4: The Right to Redress for Victims of Torture and Other Cruel, Inhuman or Degrading Punishment or Treatment (Article 5), 2017, para. 1.

[37] *Ximenes-Lopes v Brazil* (Inter-American Court of Human Rights Series C No. 149 (July 4, 2006), para. 127.

[38] *Martí de Mejía v Peru* (IACommHR, 1996), para. 157.

### 2.7 የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት

እ.ኤ.አ. በ1978 ዓ.ም. የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት በታዋቂው እና ብዙ ትችት በተሰነዘረበት በአየርላንድ እና ዩናይትድ ኪንግደም ጉዳይ ላይ የተጠረጠሩ አሸባሪዎችን ለመመርመር ጥቅም ላይ የሚውሉ የስሜት መቃወስ የሚያስከትሉ ዘዴዎችን [በእስረኛው ጭንቅላት ላይ መከለያ/መሸፈኛ ማስቀመጥ፣ ለማያቋርጥና አሰልቺ ድምጽ መገዛት፣ እንቅልፍ ማጣት፣ ምግብና ውሃ ማጣት፣ ግድግዳ ተደግፎ መቆም] ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት እንጂ ማሰቃየት አይደለም ብሎ በመወሰን ከፍ ያለ የከባድነት ደረጃ አስቀመጠ፡፡[39] ሆኖም ይህ የአየርላንድ እና ዩናይትድ ኪንግደም ጉዳይ ባለሥልጣናቱ የእምነት ቃል ለማግኘት ሲሉ የሕጋዊ የምርመራ ዘዴዎች አካል አድርገው የተጠቀሙባቸው አምስቱ ዘዴዎች በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 መሠረት የተከለከሉ ናቸው ብሎ በመወሰኑ ጠቃሚ ነው፡፡ እንዲሁም ይህ ጉዳይ ተንሸራታች የከባድነት ሚዛን ላይ የተመሰረተ ሦስት ዓይነት ክብርን ማዋረድ ያካተተ ገደብ በመፍትሔ ሐሳብነት የቀረበበት ነበር፡፡ ይህም ማሰቃየት ተፈጽሟል ለማለት ቀደም ሲል ጥቅም ላይ ይውል የነበረውን ዓላማ ተኮር አቀራረብ ተክቷል፡፡ በተመሳሳይ ራሚሬዝ ሳንቼዝ እና ፈረንሣይ ጉዳይ በ1970ዎቹ በዓለም ላይ እጅግ አደገኛ አሸባሪ ተብሎ የሚታሰበውን ራሚሬዝ ሳንቼዝ (ወይም በቅጽል ስሙ 'ካርሎስ ቀበሮው' በመባል የሚታወቀው ቬንዙዌላዊ ዜጋ) ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች ከተፈረደበት በኋላ ለብቻው ተገልሎ በመታሰር ያሳለፈውን ጊዜ (8 ዓመታት) በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ምንም ዓይነት የአንቀጽ 3 ጥሰት አልተፈጸም ብሎ ወስኖ ነበር፡፡

እንዲህ ዓይነቱ በተለየ የእስር ክፍል ውስጥ ለብቻ ማቆየት የሚያስከትለውን የረጅም ጊዜ ተጽዕኖ በተመለከተ ተገቢ ስጋቶች ቢኖሩም ፍርድ ቤቱ በተለይም የአመልካችን ባህሪይና የደቀነውን አደጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የተያዘባቸው ሁኔታዎች በአንቀጽ 3 መሠረት ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን

[39] *Ireland v United Kingdom* App no 5310/71 (ECtHR, 18 January 1978), para. 96.

የሚያዋርድ አያያዝ ለማቋቋም የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የከባድነት ደረጃ ላይ አልደረሱም የሚል አመለካከት ነበረው::[40]

ሌላው ቁልፍ የአወሳሰን መርሆዎችን ካቋቋሙ ቀደምት መሪ ጉዳዮች አንዱ የነበረው የግሪክ ጉዳይ (እ.ኤ.አ. በ1996 ውሳኔ ያገኘ) ሲሆን መስከረም 1960 ዓ.ም. ዴንማርክ፣ ኖርዌይ፣ ስዊድን እና ኔዘርላንድስ በዚያው ዓመት መባቻ ላይ ሥልጣን የያዘው የግሪክ ወታደራዊ መንግሥት የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት ጥሰቶችን ፈጽሟል በማለት ለአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ክስ አቅርበው ነበር:: እ.ኤ.አ. በ1969 የቀድሞው የአውሮፓ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ማሰቃየትን ጨምሮ ከባድ ጥሰቶችን አግኝቷል፤ ማሰቃየትን ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ለይቷል::[41] ኮሚሽኑ የግሪክ መንግሥት ለእስረኞች ምግብ፣ ውሃ፣ በክረምት ወቅት ማሞቂያ፣ ተገቢ የማጠቢያ መገልገያዎች፣ አልባሳት፣ ሕክምና እና የጥርስ ጤና መጠበቂያ ማቅረብ አለመቻሉ የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 ድንጋጌን በመጣስ የማሰቃየት ተግባር ነው ብሎ ወስኖ ነበር:: ሀገራት ለእስረኞች በቂ ምግብ፣ ውሃ፣ ሕክምና፣ አልባሳት እና የመሳሰሉትን የመስጠት ከተለያዩ ሰብዓዊ መብቶች የሚመነጩ ሕጋዊ ግዴታዎች ስላለባቸው በፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 1 ውስጥ የተደነገገው ማሰቃየት መከልከሉ ባለማድረግ የፈጸመውን አይጨምርም ብሎ መደምደም ተገቢ አይደለም:: በተመሳሳይ የፀረ ማሰቃየት ኮሚቴም ሀገራት በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ለሁለቱም ተጠያቂ መሆናቸውን አብራርቷል:: ከዚያ ቀደም ማሰቃየት ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የሚለየው ልዩ ፍሬ ነገር እንደያዘ ይቆጠር ነበር፣ ይኸውም ከተፈጥሮው ወይም ከከባድነቱ ይልቅ የተፈጸመበት ዓላማ ነበር:: ወታደራዊ መንግሥቱ ከአውሮፓ ምክር ቤት አባልነት በመውጣት ምላሽ ሰጠ:: ጉዳዩ በስምምነቱ ታሪክ

[40] *Ramirez Sanchez v France* App no 59450/00 (ECtHR, 4 July 2006).
[41] The Greek case [3321/67 (Denmark v. Greece), 3322/67 (Norway v. Greece), 3323/67 (Sweden v. Greece), 3344/67 (Netherlands v. Greece)]

ውስጥ በጣም ታዋቂ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነበር። ስለሆነም ሁሉም ማሰቃየት ኢሰብዓዊና ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ እንዲሁም ኢሰብዓዊ አያያዝ ክብርን የሚያዋርድ መሆን አለበት። ኢሰብዓዊ አያያዝ ቢያንስ ሆን ተብሎ ከባድ አዕምሮአዊም ሆነ አካላዊ ማሰቃየትን የሚያስከትልና በዚህ የተለየ ሁኔታም ተገቢ ያልሆነውን አያያዝ ያጠቃልላል ተብሎ ትርጉም ተሰጠው።

ፍርድ ቤቱ በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 ላይ የተደነገገው ስደተኞችንና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ማሳድደ ወይም ስቃይ ይደርስብናል ብለው ወደሚሰጉበት ሀገር አስገድዶ መመለስ መከልከልን ለማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ ለተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ለሆነ ወይም ክብርን ለሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ከመዳረግ አደጋ ጋር በእኩል ተፈጻሚ አድርጎታል።[42] የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴም ከሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 7 ጋር በተገናኘ ይህንኑ የፍርድ ውሳኔ ሕግ ተከትሏል።[43] በዚህ ረገድ የተባበሩት መንግሥታት የማሰቃየት ጉዳይ የሚመለከተው ልዩ ራፖርተር እንዲህ ብሏል፦ 'ሀገራት ማንንም ሰው ማሰቃየት ወይም ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ሊደርስበት ይችላል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ወዳለበት ሁኔታ እንዳይመልሱ ተከልክለዋል።[44]

የማሰቃየት ትርጓሜና የተፈጻሚነቱ ወሰንን በተመለከተ የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት ሽብርተኝነትን ለመከላከል ለሚተገበሩ ልማዳዊ አሠራሮች ወይም ለፀረ ሽብርተኝነት እርምጃዎች ልዩ ጠቀሜታ ያላቸው ሌሎች በርካታ ውሳኔዎችን ሰጥቷል። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1996 በአክሶይ እና ቱርክ ጉዳይ ላይ አመልካች እ.ኤ.አ. በ1992 የኩርዲስታን የሠራተኞች ፓርቲ አሸባሪዎችን በመርዳትና በመደገፍ ተጠርጥሮ መታሰሩን በሚመለከት አንዱ የአቤቱታው መነሻ አመልካቹ ተሰቃይቷል ወይም ልብሱ ወልቆ ራቁቱን፣ እጆቹን አንድ ላይ ከጀርባው

---

[42] *Soering v the United Kingdom* Series A no 161 (ECtHR, 7 July 1989) para. 439.
[43] Chitat Ng v Canada, No 469/1991, UN Doc CCPR/C/49/D/469/1991, 5 November 1993.
[44] United Nations Special Rapporteur on Torture (Juan Méndez) 'Report of the Special Rapporteur on Torture and Other Cruel, Inhuman or Degrading Treatment or Punishment' (2016) UN Doc A/HRC/31/57, para 33.

በማሰርና ከዚያም በእጆቹ ተንጠልጥሏል የሚል ነበር (ቅጣቱ 'የፍልስጤም ስቅላት' በመባል ይታወቃል)፡፡ ተጎጂው የእጅ አንጓዎቹ ወደኋላ በገመድ ታስረው ከመሬት ላይ ተነስቶ እና ከዚያም በፍጥነትና በድንገት በመሳብ በከፊል ወደ መሬት ወድቆ ለረጅም ጊዜ ተንጠልጥሎ እንዲቆይ የሚደረግበት የማሰቃየት ዓይነት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በአመልካች ላይ የተፈጸመው አያያዝ ከባድና ጭካኔ የተሞላበት በመሆኑ የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 ድንጋጌን የጣሰና እንደማሰቃየት ሊገለጽ ይችላል የሚል እምነት ነበረው፡፡[45]

ሌላው ፍርድ ቤቱ ከሰጣቸው ውሳኔዎች አንዱ በሆነው በአይዲን እና ቱርክ ጉዳይ (እ.ኤ.አ. በ1997) አስገድዶ መድፈር በማሰቃየት ትርጓሜ ውስጥ እንደሚካተት አረጋግጧል፡፡[46] በዚህ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቱ እንዲህ በማለት ወስኗል፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣን በእስረኛ ላይ የሚፈጽመው አስገድዶ መድፈር ወንጀል አድራጊው የተጎጂዋን የተጋላጭነትና የተዳከመ የመቋቋም አቅምን ለመጠቀም ካለው ቅለት አንጻር በተለይ ከባድና አፀያፊ የሆነ ኢሰብዓዊ አያያዝ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ በተጨማሪም አስገድዶ መድፈር በተጎጂዋ ላይ እንደሌሎች አካላዊና አዕምሮአዊ ጥቃቶች ሳይሆን በጊዜ ሒደት የማይጠፉ ጥልቅ የሥነ ልቦና ጠባሳ ጥሎ ያልፋል፤ እናም ከዚህ ዳራ አንጻር ፍርድ ቤቱ አካላዊና አዕምሮአዊ ጥቃቶች መከማቸታቸው … በተለይም የተፈጸመባት ጭካኔ የተሞላበት የአስገድዶ መድፈር ድርጊት የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 ድንጋጌን በመጣስ ማሰቃየት እንደሆነ ያምናል፡፡

በአየርላንድ እና ዩናይትድ ኪንግደም ጉዳይ ላይ የተወሰነው ከፍ ያለ የከባድነት ደረጃ አሁን ተፈጻሚነት የለውም፡፡[47] በአሁኑ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የሚጠቀመው

---

[45] *Aksoy v Turkey* App no 21987/93 (ECtHR, 18 December 1996), para. 96.

[46] *Aydin v Turkey* App no 57/1996/676/866 (ECtHR, 25 September 1997).

[47] በተመሳሳይ እ.ኤ.አ. በ1997 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀረ ማሰቃየት ኮሚቴ መከለያ/መሸፈኛ የማሰቃየት ተግባር እንደሆነ ደምድሟል፤ ይህንኑ አቋም እ.ኤ.አ. በ2004 ዓ.ም. የኮሚቴው ልዩ ራፖርተር "ከተጠረጠሩ አሸባሪዎች መረጃ ለማግኘት ጥቅም ላይ በዋሉ እና ችላ ተብለው የታለፉ የተወሰኑ ዘዴዎች ላይ መረጃ ከተቀበለ በኋላ" በማለት በድጋሚ ገልጿል።

መስፈርት የተቀመጠው ሐምሌ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. በሰልማኒ እና ፈረንሳይ ጉዳይ ነበር።[48] ፍርድ ቤቱ በፀረ ማሰቃየት ስምምነት የሰፈረውን የማሰቃየት ትርጓሜን ለመጀመሪያ ጊዜ የጠቀሰበትና ዓላማ ወሳኝ ፍሬ ጉዳይ ነው በማለት ወደ ቀድሞ አቋሙ የተመለሰበት ጉዳይ ነበር። በዚህ ጉዳይ፦ አሕመድ ሰልማኒ የተባለ ትውልደ ኔዘርላንድስ ግን የሞሮኮ ዜጋ ሲሆን ኅዳር 15 ቀን 1984 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሀገር በፓሪስ ከተማ ውስጥ በአንድ ሆቴል ላይ በተደረገ ክትትል በአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር ወንጀል ተጠርጥሮ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ የፖሊስ አባሉ ወንጀሉን በግድ እንዲያምን ለማድረግ ለሦስት ቀናት በፈጀ ጥቃት ሰልማኒን ደበደበው፣ አስፈራራውና አዋረደው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ተጠርጣሪው ተደጋጋሚ ከባድ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ይደርስበት ነበር፤ ይኸውም በተደጋጋሚ በቡጢ፣ በእርግጫ እና በዕቃዎች (የቤዝቦል ኳስ መምቻ ዱላን ጨምሮ) ተመቷል፣ የፖሊስ አባሉ ሽንቱን እላዩ ላይ ሸናበት፣ በመበየጃና በሐኪም መርፌ አስፈራው፤ በተጨማሪም ሌላ የፖሊስ አባል ዱላውን/በትሩን ተጠቅሞ በፊንጢጣው በኩል አስገድዶ ደፍሮት እና "እናንተ አረቦች ስትሰቃዩ ትዝናናላችሁ" ብሎ ተናግሮት ነበር። የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ሰልማኒ የአሥራ ሦስት ዓመት ጽኑ እስራት ተፈርዶበት በሞሜዲ ከተማ በሚገኝ እስር ቤት ውስጥ ይገኝ ነበር። ይህን አካላዊና አዕምሮአዊ ጥቃት እንደማሰቃየት ለመመደብ በበቂ ሁኔታ ከባድ ነበር።[49] ፍርድ ቤቱ ከክሱ አሳሳቢነት እና ካለፈው ጊዜ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣናቱ ምርመራውን በፍጥነት ለማጠናቀቅ ሁሉንም አዎንታዊ እርምጃዎች አልወሰዱም ብሎ በመደምደም የፈረንሣይ መንግሥት ያቀረበለትን የመከላከያ መልስ ውድቅ አደረገ። ፍርድ ቤቱ አክሎም አንድ ግለሰብ በጥሩ ጤንነት ላይ ወደ ፖሊስ ከተወሰደ በኋላ ነገር ግን በሚለቀቅበት ጊዜ ጉዳት ደርሶበት ከተገኘ ጉዳቱ እንዴት እንደተከሰተ አሳማኝ ማብራሪያ እንዲሰጥ ግዴታ አለበት፤ ይህ ካልሆነ ግን የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 ድንጋጌን ይጥሳል ሲል አመከነየ (ውሳኔውን በምክንያት አስደገፈ)። በሰልማኒ እና

---

[48] *Selmouni v France* App no 25803/94 (ECtHR, 28 July 1999).

[49] ዝኒ ከማሁ

ፈረንሳይ ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በበርካታ ምክንያቶች ጥልቅ ነው፤ በተለይም ፍርድ ቤቱ አጽንኦቱን ከተከሳሹን ባህሪይ ወደ ተጠርጣሪው ስቃይ በመለወጥ በአንቀጽ 3 ላይ የትርጓሜ ዕድገት በማሸጋገር አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። ፍርድ ቤቱ ማሰቃየት እና ኢሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ በፍፁም የተከለከሉ መሆናቸውን ጉልህ በሆነ መልኩ ገልጿል፤ እንዲሁም የሀገሪቱን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ቢያጋጥም እንኳ ከዚህ ክልከላ ማፈንገጥ አይቻልም።

በሰልማኒ እና ፈረንሳይ ጉዳይ ላይ ከተሰጠው ውሳኔ አኳያ ሲታይ ከዚህ በላይ የተገለጹት እና በተለይ መስከረም 1 ቀን 1994 ዓ.ም. በአሜሪካ ሀገር ውስጥ ከተፈጸመው ጥቃት (በተለምዶ 9/11 በመባል ይታወቃል) ጀምሮ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በተለያዩ ሀገራት ሲተገበሩ የነበሩ የስሜት መቃወስ የሚያስከትሉ ዘዴዎች የማሰቃየት ተግባራት እንደሆኑ ግልጽ ነው።[50] በአጠቃላይ እንደ አሜሪካና እስራኤል ያሉ አንዳንድ ሀገራት ከጥቃቱ በኋላ ማስገደድ ያለባቸው የወንጀል ምርመራ ዘዴዎችን ይበልጥ ፈቃጅ የሆነ አካሄድን መከተል መርጠዋል። ሆኖም በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለው ማንኛውም የደኅንነት ኤጀንሲ የሚጠቀማቸው ትክክለኛ ስልቶች በጣም ምስጢራዊ እና ለተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ ተደራሽ ናቸው።[51]

በአካላዊም ሆነ በአዕምሮአዊ ማሰቃየት መካከል ምንም ልዩነት የለም። ስለዚህ ማሰቃየት እፈጽማለሁ ብሎ በማስፈራራት ብቻ ከባድ የሥነ ልቦና ስቃይ ማድረስ እንደማሰቃየት ይቆጠራል።[52]

---

[50] Manfred Nowak et. al. (n 18); Report of the Committee against Torture (1997), para. 257; Ogechi Joy Anwukah, 'The Effectiveness of International Law: Torture and Counterterrorism' Annual Survey of International & Comparative Law: Vol. 21: Iss. 1, Article 4.

[51] Yuval Ginbar, 'Chapter 25. Torture in the 21st century: three stories, three lessons' in Malcolm D. Evans and Jens Modvig (eds.), *Research Handbook on Torture: Legal and Medical Perspectives on Prohibition and Prevention*, (Edward Elgar Publishing Limited, 2020).

[52] *Akkoc v Turkey* App Nos. 22947 and 22948/93 (ECtHR, 10 October 2000), para. 116.

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

በማሰቃየት ላይ በሰፊው ያነጋገረው የጋፍገን እና ጀርመን ጉዳይ (እ.ኤ.አ. በ2010) ነበር። ይኸውም እ.ኤ.አ. በ2002 ፖሊስ የተጎጂውን ሕይወት ለማትረፍ (ተጠልፎ የተወሰደ ልጅን ለማዳን) ሲል በምርመራ ወቅት ማግነስ ጋፍገን የተባለ ግለሰብ ሕፃንን በመግደል ወንጀል ተጠርጥሮ ተይዞ ለምርመራ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከመጣ በኋላ የማሰቃየት ዛቻ አድርሶበታል፤ በዚህም ምክንያት ተጠርጣሪው/አመልካቹ የተጎጂው አካል /አስክሬን/ የሚገኝበትን ቦታ ተናግሯል መባሉ ውዝግብ አስነስቷል። ተጠርጣሪው/አመልካቹ የተጎጂው የሚገኝበትን ቦታ ለመግለጽ ፈቃደኛ ካልሆነ ሌላ ለዚህ ዓይነቱ ዓላማ በልዩ ሁኔታ የሰለጠነ ሰው ሊቋቋመው የማይችለው ሕመም እንደሚያደርስበት በፖሊስ አባል ማስፈራራት ደርሶበት ነበር። ምክትል የፖሊስ አዛዡ ተጠርጣሪውን/አመልካቹን እንዲያስፈራሩት ወይም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የኃይል እርምጃ እንዲወስዱበት ለበታች ታዛዥ የፖሊስ አባላት በተደጋጋሚ ትዕዛዝ በመስጠቱ ምክንያት ትዕዛዙ እንደድንገተኛ ድርጊት ሊቆጠር አይችልም፤ ይልቁንም አስቀድሞ የታቀደ እና የተሰላ ነው። የፖሊስ አባላቱ የተጎጂውን ሕይወት አሁንም ማዳን እንደሚቻል ባመኑ ጊዜ በተጠርጣሪው/በአመልካቹ ላይ በደል እንደሚያደርሱበት በማስፈራራት የተደረገው ምርመራ በከፍተኛ ውጥረት እና ስሜት በተሞላበት ድባብ ውስጥ ለአስር ደቂቃ ያህል ቆይቶ ነበር። ተጠርጣሪው/አመልካቹ እጁ በካቴና ታስሮ ስለነበር የተጋላጭነት ሁኔታ ውስጥ ነበር። ስለዚህ የደረሰበት ዛቻ ከፍተኛ ፍርሃት፣ ጭንቀትና የአዕምሮ ስቃይ የግድ ያስከትልበታል። የፖሊስ አባላቱ ድርጊቱን የፈጸሙበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት የአንድ ግለሰብ ሕይወት አደጋ ላይ በሚወድቅበት ሁኔታ ውስጥ እንኳ ማሰቃየት እና ኢሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ሊፈጸም እንደማይቻል በድጋሚ ገልጿል። አመልካቹ የተፈጸመበት/የተገደደበት የምርመራ ዘዴ በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 የተከለከለውን ኢሰብዓዊ ድርጊት ተደርጎ ለመቆጠር በበቂ ሁኔታ ከባድ ሆኖ ተገኝቷል።[53] ስለሆነም የጠፋው ልጅ የት እንዳለ ለማወቅ ሲባል በፖሊስ የተፈጸመ የአካል ጉዳት ማስፈራሪያ ጥሰት ነው። የማሰቃየት ዛቻ እንደማሰቃየት

[53] *Gäfgen v Germany* App no 22978/05 (ECtHR, 1 June 2010).

 DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.8

ሊቆጠር ይችላል ምክንያቱም የማሰቃየት ባህሪይ ሁለቱንም አካላዊና አዕምሮአዊ ስቃይን ይሸፍናል።

### 2.8 የኡጋንዳ የፀረ ማሰቃየት ሕግ ማዕቀፍ

በሀገር ደረጃ ኡጋንዳ በአፍሪካ ውስጥ ጠንካራ ፀረ ማሰቃየት የሕግ ማዕቀፍ ካላቸው ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ ናት።[54] የኡጋንዳ መንግሥት እ.ኤ.አ. በ1986 የፀረ ማሰቃየት ስምምነትን አጽድቋል። እንዲሁም የኡጋንዳ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 24 ማሰቃየትን፣ ጭካኔ የተሞላበት ኢሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝና ቅጣትን ይከለክላል። በተጨማሪም ማሰቃየትን እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣትን ለመከላከል በወጣው ስምምነት አንቀጽ 1(2) ላይ በተደነገገው መሠረት እ.ኤ.አ. በ2012 ዓ.ም. በኡጋንዳ ሀገር ማሰቃየትን ለመከላከልና ለመከልከል የወጣው ሕግ የማሰቃየት ትርጓሜን በማስፋት ግለሰቦችን እንዲያካትት አድርጓል።[55] ለኡጋንዳ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የቀረቡ ብዙዎቹ አቤቱታዎች ላይ ማሰቃየትን የሚመስሉ ድርጊቶች የተፈጸሙት ከፖሊስ ቀጥሎ በግለሰቦች ከመሆኑ አንጻር ይህ ትርጓሜ እጅግ በጣም የሚያስደስት እርምጃ ወይም ሰፊ የተፈጻሚነት ወሰን የያዘ ብሔራዊ ሕግ ነው።[56] እ.ኤ.አ. በ2019 በኢሳ ዋዜምቤ እና በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መካከል በነበረው ክስ ላይ የሀገሪቱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማሰቃየትን ፈጽሞ "መታገስ እንደማይቻል" በመግለጽ ከማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ነፃ የመሆን መብት ፍፁምና መጣሱ በማንኛውም ሁኔታ ምክንያት ሊቀርብበት የማይችል መብት ነው ሲል

---

[54] REDRESS and the Convention against Torture Initiative (CTI), *Anti-Torture Standards in Common Law Africa: Good Practices and Way Forward* <https://www.google.com/url?sa=t&source=web&rct=j&opi=89978449&url=https://redress.org/wp-content/uploads/2022/04/06.04.2022-CTI-REDRESS-Anti-Torture-Law-Standards-in-Africa_Report_WEB.pdf&ved=2ahUKEwjp_dis6eWIAxXHS_EDHU0YDZsQFnoECBQQAQ&usg=AOvVaw13zI3p_wWKNTRRm_SaOVIV> accessed on September 4, 2024.

[55] Article 2(1) of Prevention and Prohibition of Torture Act 3 of 2012

[56] African Center for Treatment and Rehabilitation of Torture Victims (ACTV), 'THE SITUATIONAL ANALYSIS ON THE PREVALENCE OF TORTURE IN UGANDA', 2015, p. 83.

ወሰነ፡፡ ይህ ውሳኔ እንደ ጥሩ ልምድ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡[57] ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ውስጥ የማሰቃየት ተግባራት ጨምረዋል የሚሉ ሪፖርቶች በተደጋጋሚ ወጥተዋል፡፡[58]

### 2.9 ማሰቃየትን የተመለከተ የሕግ ማዕቀፍና አተገባበሩ በኢትዮጵያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ መጋቢት 5 ቀን 1986 ዓ.ም. የፀረ ማሰቃየት ስምምነትን ተቀብላ አጽድቃለች፡፡ ሆኖም የፀረ ማሰቃየት ስምምነቱን አማራጭ ፕሮቶኮል ፈራሚ አባል ሀገር አይደለችም፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 18 ሁሉም ሰው ከማሰቃየትና ሌላ ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ይህ መብት በማናቸውም ሁኔታ ሊጣስ አይችልም ምክንያቱም ድንጋጌው ምንም ዓይነት ልዩ ሁኔታን አላስቀመጥም፡፡ ምንም እንኳ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 28(1) ላይ 'ቶርቸር' የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ወደ አማርኛ 'ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊት' ተብሎ ቢተረጎም ሰብዓዊ የድብደባ ድርጊት የሚባል በሕግ የተፈቀደ አድራጎት የለም፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግን[59] ጨምሮ ሌሎች የሀገሪቱ ሕግጋት በፀረ ማሰቃየት ስምምነቱ አንቀጽ 1 ላይ በተቀመጠው ትርጓሜ መሠረት 'ማሰቃየት' ለሚለው ቃል የተሟላ ትርጓሜ አያስቀምጡም፡፡ ነገር ግን ሀገሪቱ ይህን ስምምነት በማጽደቋ ምክንያት በስምምነቱ ላይ የሰፈረው የማሰቃየት ትርጓሜ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የሕግ ባለሙያዎች ማንኛውም የማሰቃየት ተግባር ኢሰብዓዊ፣ ጭካኔ የተሞላበትና ክብርን የሚያዋርድ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 18(1) ላይ ዕውቅና ተሰጥቶታል ቢባልም ይሄ ድንጋጌ ብቻውን በቂ አይደለም

---

[57] Issa Wazembe v. Attorney General (CIVIL SUIT NO. 154 OF 2016) [2019] UGHCCD 181 (19 August 2019)

[58] Uganda Human Rights Commission (UHRC) Annual Reports of 2021 – 2023; OMCT, *Uganda: Increase in torture cases despite a strong legal framework* <https://www.omct.org/en/resources/reports/uganda-increase-in-torture-cases-despite-a-strong-legal-framework-2> accessed on August 31, 2024.

[59] አንቀጽ 424 ላይ 'የአካልና የመንፈስ ስቃይ' የሚል ሐረግ ሰፍሯል።

 DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.8

ሲሉ ይሞግታሉ::[60] ለዚህም እንደምክንያት የቀረበው ማሰቃየት ልዩ ባህሪያት ስላሉት እና ይህ ድንጋጌ የተጠያቂዎቹን ኃላፊነት በግለሰብ ደረጃ ብቻ ያስቀረዋል የሚል ነው፤ ስለሆነም ሀገሪቱ ራሱን የቻለ ተጨማሪ ብሔራዊ የፀረ ማሰቃየት ሕግ ማውጣት አለባት ሲሉ አጥብቀው ይከራከራሉ:: በተጨማሪም ማሰቃየት እስካልቀጠለ ድረስ ሀገሪቱ የፀረ ማሰቃየት ስምምነቱን አማራጭ ፕሮቶኮልን ልትፈርምና ልታጸድቅ ይገባል የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ::

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ይፋ ባደረገው ሦስተኛው ዓመታዊ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት[61]፣ ጥቅምት 23 ቀን 2016 ዓ.ም. ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ[62] እንዲሁም ሚያዚያ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. የማሰቃየት ጉዳይ ለሚመለከተው ልዩ ራፖርተር ባቀረበው አስተያየት[63] ላይ እንደተገለጸው ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ለሕዝብ በግልጽ በማይታወቁ (ወይም ምስጢራዊ በሆኑ) እስር ቤቶች ወይም በወታደራዊ ካምፖች ውስጥ ብዙን ጊዜ የአስገድዶ መሰወር ድርጊት ዒላማ በሆኑት የፖለቲካ ተቃውሞ ባላቸው ሰዎች ላይ ማሰቃየትና ሌላ ኢሰብዓዊ አያያዝና ቅጣት ስልታዊ በሆነ መንገድ መፈጸማቸውን የሚያሳይ ማስረጃ መገኘቱና ያለምንም ተጠያቂነት እንደዚህ ያለ ከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የመፈጸም አዝማሚያ መስተዋሉ አሁንም በጣም አሳሳቢ ነው መባሉ ያስደነግጣል::

---

[60] *ውብሸት ሙላት፣ ለአገራዊ መግባባት የፀረ ማሰቃየት (ቶርቸር) ሕግ አስፈላጊነት* <https://www.ethiopianreporter.com/50707/> accessed on January 22, 2018.

[61] ኢሰመኮ፣ *የኢትዮጵያ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም.*፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ሰኔ 2016 ዓ.ም.

[62] ኢሰመኮ፣ *አዲስ አበባ፦ "ለ7 ወራት ገደማ ተይዤ በቆየሁበት ወታደራዊ ካምፕ ሌሎች 60 የሚጠጉ ሰዎች ተይዘው እንደነበር ተመልክቻለሁ"* <https://ehrc.org/%E1%8A%A0%E1%8B%B2%E1%88%B5-%E1%8A%A0%E1%89%A0%E1%89%A3%E1%8D%A1-%E1%88%887-%E1%8B%88%E1%88%AB%E1%89%B5-%E1%8C%88%E1%8B%B0%E1%88%9B-%E1%89%B0%E1%8B%AD%E1%8B%A4-%E1%89%A0%E1%89%86%E1%8B%A8/> accessed on November 1, 2024.

[63] Ethiopian Human Rights Commission Input for the Special Rapporteur on Torture፡ Identifying, Documenting, Investigating and Prosecuting Crimes of Sexual Torture Committed during War and Armed conflicts, and Rehabilitation for Victims and Survivors: the case of Ethiopia, 24 April 2024.

በተለይም ኢሰመኮ በ2016 ዓመታዊ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርቱ ላይ ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 6/2015 አተገባበር ጋር የተያያዘ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ከሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ከኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ውጪ ለጅምላ እስር ተዳርገው በተለያዩ መደበኛ ባልሆኑ ቦታዎች እና ከመኖሪያ አካባቢያቸው ርቀው የኤርትራ ስደተኞችንና ፍልሰተኞችን ጨምሮ በወቅቱ ተይዘው የታሰሩ ሰዎችን በተመለከተ የኢሰብዓዊ አያያዝ እና የማሰቃየት ተግባራት አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮች እንደነበሩ እና እስከ መስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ ለተራዘመ ጊዜ የመጎብኘት መብታቸውን የተነፈጉ እና በየትኛው ማቆያ ቦታ እንደሚገኙ ያልታወቀ ሰዎች እንደነበሩ ተጠቅሷል።[64]

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ ታይተው ሊወሰኑ የሚችሉ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሦስት ስር የተዘረዘሩትን ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር ሲል ተገቢ ውሳኔ፣ ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ተደንግጓል።[65] በዚህም መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ የፀረ ሽብርና ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች ችሎት ተቋቁሟል።[66] ከዚህም ባለፈ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኢሰመኮ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ግለሰቦች ያቀረቡትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አቤቱታ መርምሮ የምርመራውን ውጤት እንዲያቀርብ *ትዕዛዝ* ሲሰጥ ይስተዋላል፤ ኢሰመኮም የምርመራ ሪፖርት የሚያቀርብ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በምርመራው ግኝቶች መሠረት ተፈጽመዋል የተባሉት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ በገለልተኛ ቡድን ተጨማሪ ምርመራ/የወንጀል ምርመራ እንዲካሄድ ሲያዝዝ ወይም የድርጊቱ ፈጻሚ የሆኑት የፀጥታና ደኅንነት ኃይል አባላት ተይዘው ለፍትሕ ሲቀርቡና ሕጋዊ የእርምት

---

[64] ኢሰመኮ፣ የኢትዮጵያ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት (n. 61)፣ ገጽ 40 – 44 ይመለከቷል።
[65] የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 11(3) [ሃያ ሰባተኛ ዓመት፣ ቁጥር 26፣ ሚያዚያ 18 ቀን 2013 ዓ.ም.] ይመለከቷል።
[66] ለአብነት ያህል https://ethiopiainsider.com/2023/11183/ ይመልከቱ።

እርምጃ ሲወስድባቸው አይስተዋልም::[67] ሆኖም ይሄ አሠራር ኢሰመኮ በሕግ ከተሰጠው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አቤቱታዎችን የመመርመርና የመፍትሔ ሐሳብ ብቻ የመስጠት ሥልጣን[68] አንጻር ሲታይ የግብር ይውጣ መፍትሔ በመሆኑ አጥጋቢ ውጤት ሊያመጣ አይችልም:: ምክንያቱም ይኸው የመፍትሔ ሐሳብ ለተፈጸመው ጥሰት ምክንያት የሆነው ድርጊት ወይም አሠራር እንዲቆም፣ ለጥሰቱ ምክንያት የሆነው መመሪያ ተፈጻሚነቱ እንዲቀር፣ የተፈጸመው የፍትሕ መጓደል እንዲታረም ወይም ተገቢ የሆነ ማንኛውም ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ በግልጽ ከማመላከት ያለፈ አይሆንም:: አሁንም በዚህ አሠራር አማካይነት ከማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝና ቅጣት የመጠበቅ መብትን ተግባራዊነት ማረጋገጥ ባለመቻሉ ማሰቃየትን በራሱ መርምሮ የሚወስን ተጨማሪ ብቁ ችሎት ያስፈልጋል:: በእርግጥ ኢሰመኮ ባቀረበው የምርመራ ሪፖርት ላይ የሚመለከተው አካል በተሰጡት አስተያየቶችና ምክረ ሐሳቦች ላይ ሪፖርቱ በደረሰው በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ያለበቂ ምክንያት እርምጃ አለመውሰዱ ወይም እርምጃ የማይወስድበትን ምክንያት አለመግለጽ የሚያስቀጣ መሆኑን ልብ ይሏል::[69] ፀሐፊው የማሰቃየት ተግባርን ወንጀል የሚያደርግ የተለየ ሕግ ከማውጣትና ብሔራዊ የመከላከያ ዘዴ (National Preventive Mechanism) ከማቋቋም ባሻገር በኢትዮጵያ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ውስጥ ማሰቃየትን በራሱ መርምሮ የሚወስን ተጨማሪ ብቁ ችሎት አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል::

## 2.10 ማሰቃየት በፍፁም መከልከሉ አስፈላጊ ስለመሆኑ የሚቀርቡ መከራከሪያዎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ማሰቃየት በፍፁም መከልከሉ አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጹ በርካታ የተለያዩ አሳማኝ መከራከሪያዎች ይብራራሉ::

---

[67] ለአብነት ያህል https://www.google.com/amp/s/amharic.voanews.com/amp/addis-ababa-court/7140706.html ይመልከቱ።

[68] የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 210/1992 አንቀጽ 26(2)(3) [ስድስተኛ ዓመት፣ ቁጥር 40፣ ሰኔ 27 ቀን 1992 ዓ.ም.] ይመለከቷል።

[69] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 41(2) ይመለከቷል።

### 2.10.1 የሰው ልጅ በሙሉ ተፈጥሯዊ ክብር ያለው መሆኑ

ማሰቃየት የሰው ልጅን ክብር በቀጥታ መጣስ ነው፡፡ በሰው ልጅ ላይ የሚደርስ ጥቃት ነው ምክንያቱም በተጎጂዎቹ ላይ ብቻ ሳይሆን በቤተሰቦቻቸውም ላይ መከራ ያመጣል፡፡ ሰውን እንደዕቃ ይመለከታል፣ ደኅንነቱን ለሌላው ፍፁም ኃይል አሳልፎ ይሰጣል፡፡ ከአካላዊ ጉዳት በተጨማሪ ማሰቃየት ሥልጣንን አላግባብ እስከመጨረሻው በመጠቀም አንድን ሰው የተዋረደ፣ አቅመ ቢስ እና ብልሹ ያደርገዋል፡፡ ወርቃማውን ሕግ ቀላል የሰብዓዊ መብቶች መርሆ አድርገን ብንመለከተው ማሰቃየት በሰብዓዊ መብቶች መመዘኛዎች መሠረት ፈጽሞ የማይቃረን ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ይሆናል፡፡ ከዝነኛው ጀርመናዊ ፈላስፋ ከኢማኑኤል ካንት ሦስቱ ዘመን አይሽሬ የሐሳብ ቀመሮች መካከል ሁለተኛው ጽንሰ ሐሳብን ማለትም በማናቸውም ሁኔታ ትክክል የሆነውን ነገር የማድረግ በምንም ቅድመ ሁኔታ ያልተገደበና ዓለም አቀፋዊ አስገዳጅነት ያለው የሞራል ግዴታን (*Categorical Imperative*)[70] መጥቀስ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይኸውም እንዲህ ይነበባል፡ "ሁልጊዜ ሰብዓዊነትን በራስህም ሆነ በሌላው ሰውነት በምትይዝበት መንገድ፣ በፍፁም ለመጨረሻው ግብ እንደመንገድ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም በተመሳሳይ ጊዜ በራሱ የመጨረሻው ግብ አድርገህ፣ ተግብር፡፡" በሌላ አገላለጽ አንድ ሰው የራሱንም ሆነ የሌሎችን ሰብዓዊነት ለሌላ ዓላማ ብቻ ያለመጠቀም ፍፁም ግዴታ አለበት፡፡ አንድ ሰው ሌላውን ሰው እንደአማራጭ መንገድ የመመልከት የመጠቀም መብት አለው ብሎ ማሰብ አይችልም፡፡ ማሰቃየት ፈጽሞ መከልከል አለበት ምክንያቱም አንድ ሰው በሌላው ላይ ሊፈጽም የሚችላቸውን አስከፊ ድርጊቶች ይዟል፡፡ አሰቃይ ለመሆን አንድ ሰው ተፈጥሯዊ ርህራሄን እና ለራሱ ያለውን ግምትን ማፈን እና በምትኩ ሰውን ለማሰቃየት የሚያሰላ ማሽን መሆን አለበት፡፡[71]

[70] Immanuel Kant, *Groundwork of the Metaphysics of Morals* (translated and analyzed by H.J. Paton in The Moral Law) (Hutchinson, London, 1972), p. 91.
[71] Yuval Ginbar, *Why Not Torture Terrorists?* (Oxford University Press, New York, 2008) pp. 64-88.

### 2.10.2 የማሰቃየት ተግባር ሰለባ በሆኑ ተጎጂዎች ላይ አሰቃቂ መዘዞች ማስከተሉ[72]

የፀሐፊው ልምድ እንደሚያስረዳው የማሰቃየት ተግባር በተጎጂዎች ላይ የቅርብና የረጅም ጊዜ አካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ተጽዕኖ ያስከትላል:: የማሰቃየት ሰለባዎች የጤና እክል፣ የአካል ጉዳት እና አንዳንዴ ለሞት ይዳረጋሉ:: ማሰቃየት በተጎጂዎች ላይ የማይጠፋ አሰቃቂ የስሜት ቀውስ ጥሎ ያልፋል:: ማሰቃየት የሚያስከትላቸው መዘዞች ብዙውን ጊዜ እጅግ አሰቃቂ ከመሆናቸው ባሻገር ወዲያውኑ ከሚሰማ ሕመም በላይ ይደርሳሉ:: ብዙ ተጎጂዎች በድኅረ አሰቃቂ የሥነ ልቦና ጭንቀት (በአዕምሮ ሕመም) ይሰቃያሉ:: ምልክቶቹም ያለፈው መጥፎ ክስተት በአዕምሮ ውስጥ ድንገት እየመጣ የሚረብሽ ትውስታ፣ ከባድ ጭንቀት፣ እንቅልፍ ማጣት፣ ቅዠት፣ ድብርት፣ የማስታወስ ችግር፣ የመሳሰሉት ናቸው:: የማሰቃየት ሰለባዎች ብዙውን ጊዜ ባሳለፉት ውርደት ምክንያት የጥፋተኝነት ስሜትና ሀፍረት ይሰማቸዋል:: ብዙዎች እራሳቸውን ወይም ጓደኞቻቸውን እና ቤተሰባቸውን እንደከዱ ይሰማቸዋል:: እነዚህ ሁሉ ምልክቶች ላልተለመደና ኢሰብዓዊ አያያዝና ቅጣት የተለመዱ ሰዋዊ ምላሾች ናቸው::

---

72 *Effects of Torture* <https://www.cvt.org/resources/effects-of-torture/#:~:text=Long%2Dterm%20psychological%20effects%20include,traumatic%20stress%20disorder%20(PTSD).> accessed on August 30, 2024; Amanda C de C Williams and Jannie van der Merwe, 'The psychological impact of torture', [2013] 7(2) British Journal of Pain <https://www.ncbi.nlm.nih.gov/pmc/articles/PMC4590125/> accessed on August 27, 2024; Danie Meyer-Parlapanis and Thomas Elbert, 'Psychology of Torture and its Consequences' [2015] University of Konstanz <https://kops.uni-konstanz.de/entities/publication/019e3184-3747-4545-bd98-f1b4cef48e21> accessed on August 26, 2024.

### 2.10.3 የተፈለገውን ውጤት የማያስገኝ ኢ-ሳይንሳዊ ዘዴ መሆኑ[73]

በአሜሪካ ማዕከላዊ የደኅንነት መረጃ /የስለላ/ ኤጀንሲ (ሲአይኤ) ሲተገበር በነበረው ኤምኬ-አልትራ የተባለው ምስጢራዊ ፕሮጀክት (*Project MKUltra*) እንዳመላከተው ማሰቃየት መረጃ ለመሰብሰብ ውጤታማነቱ በሳይንስ አልተረጋገጠም::[74] ማሰቃየት መፈጸም በደንብ የታሰበ ቢሆንም በመጨረሻ ግን የተፈለገውን ወጤት የማያመጣ ዘዴ ነው:: የቆዩና የቅርብ ጊዜ ለሰብዓዊ መብቶች ችሎቶች የቀረቡ ጉዳዮችን ስንመለከት አብዛኛውን ጊዜ በማሰቃየት የተገኘ መረጃ ለውጤታማ የወንጀል ምርመራ አስተዋጽኦ አይኖረውም:: አንደኛ፣ አንድ ሰው ማሰቃየት በሚፈጸምበት ጊዜ ስቃዩን ለማስቆም ሲል ብቻ መርማሪው እንዲልለት የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር፣ እውነት ቢሆንም ባይሆንም፣ ማመን ይቀናዋል:: ንፁህ የሆነውን ሰው ያላደረገውን ነገር እንዲያምን ማድረግ ትክክለኛ ወንጀል አድራጊው ለፍርድ አልቀረበም ማለት ነው:: በዚህም የተነሳ ተጎጂዎቹን የበለጠ ቂመኛ ከማድረጉም ባሻገር ለበቀል ያነሳሳቸዋል:: ሁለተኛ፣ በማሰቃየት የተገኙ መግለጫዎች ወይም

---

[73] Shane O'Mara, *Why Torture Doesn't Work: The Neuroscience of Interrogation* (Harvard University Press, 2015), pp. 174-185; *5 Reasons Why Torture Does Not Work and Can Never Be Justified* <https://www.humanrightscareers.com/issues/reasons-why-torture-does-not-work/#:~:text=1%20Torture%20is%20an%20Ineffective%20Interrogation%20tool&text=Usually%2C%20the%20application%20of%20physical,to%20end%20the%20painful%20experience.> accessed on August 30, 2024; *Why is torture wrong?* <https://www.bbc.co.uk/ethics/torture/ethics/wrong_1.shtml> accessed on August 29, 2024; *The prohibition against torture and its pragmatic effects* <https://www.publicinternationallawandpolicygroup.org/lawyering-justice-blog/2023/6/9/the-prohibition-against-torture-and-its-pragmatic-effects> accessed on August 29, 2024; *Torture is ineffective in getting information* <https://www.indystar.com/story/opinion/readers/2014/12/17/guantanamo-bay-detention-center-torture-letter-to-editor/20552437/> accessed on August 30, 2024; M. Usman, 'Torture as an Ineffective Tool of Demoralization in Jean Paul Sartre's Men Without Shadows' [2019] 1(2) International Journal of English Language Studies <https://al-kindipublisher.com/index.php/ijels/article/view/117> accessed on August 29, 2024.

[74] Stephen Kinzer, *Poisoner in Chief: Sidney Gottlieb and the CIA Search for Mind Control* (Henry Holt & Co, New York, 2019); Adam D. Jacobson, 'Back to the Dark Side: Explaining the CIA's Repeated Use of Torture' 33:2 Terrorism and Political Violence <https://www.tandfonline.com/doi/abs/10.1080/09546553.2021.1880193> accessed on August 29, 2024; Rupert Stone, 'Science Shows That Torture Doesn't Work and Is Counterproductive', Newsweek, (May 8, 2016) <http://www.newsweek.com/2016/05/20/science-shows-torture-doesnt-work-456854.html> accessed on August 29, 2024.

እውነተኛ ማስረጃዎች በወንጀል ክስ ክርክሮች ላይ ሊጠቅሙ አይችሉም::[75] ሦስተኛ፣ የፖሊስ አባላት በማሰቃየት ላይ የሚተማመኑ እንደሆነ የበለጠ አስተማማኝ ማስረጃ እንዲያገኙ የሚረዳ ሙያዊ ክህሎታቸውን ማሳደግ አይችሉም::

### 2.10.4 የፖሊስ ኃይል አጠቃቀምን የሚገዙ የአስፈላጊነትና የተመጣጣኝነት ጥብቅ መስፈርቶች መኖራቸው

የፖሊስ አባላት ኃይልን ከመጠን በላይ ከተጠቀሙ ማሰቃየት ሊያስከትል ይችላል:: ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ሊፈጽምባቸው ከሚችሉ ሁኔታዎች መካከል ተጠርጣሪዎችን በካቴና ማሰር (በቁጥጥር ስር በሚውሉበት ጊዜም ሆነ ከታሰሩ በኋላ)፣ ተቃውሞን ለማሸነፍ አካላዊ ኃይል መጠቀም ወይም የጦር መሣሪያ መጠቀም ይገኙበታል:: አብዛኛው የፖሊስ ሥራ ኃይል መጠቀምን አያስከትልም:: የፖሊስ ተግባራትን ለማከናወን የኃይል አጠቃቀም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እና ከሚያስፈልገው መጠን ያላለፈ እንደሆነ ተገቢ ይሆናል::

ፖሊስ አግባብነት ያላቸው የተግባቦት ክህሎቶችን በመጠቀም በመጀመሪያ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለበት:: እነዚህ ሰላማዊ መንገዶች ውጤታማ ካልሆኑ ወይም የታሰበውን ውጤት ለማሳካት አቅም የሌላቸው እንደሆነ ብቻ አካላዊ ኃይል መጠቀምን ጨምሮ በሰብዓዊ መብቶች ላይ የበለጠ ጣልቃ ገብ የሆኑ ዘዴዎችን ሊተገበሩ ይችላሉ:: ሕይወት አደጋ ላይ ከወደቀ ግን ገዳይ የጦር መሣሪያዎችን እንደ የመጨረሻ አማራጭ ብቻ መጠቀም አለበት::

[75] የፀረ ማሰቃየት ስምምነት አንቀጽ 15 ይመለከቷል። Tobias Thienel, 'The Admissibility of Evidence Obtained by Torture under International Law' [2006] 17/2 EJI <https://papers.ssrn.com/sol3/papers.cfm?abstract_id=1092712 > accessed on August 25, 2024; Convention against Torture Initiative (CTI), *NON-ADMISSION OF EVIDENCE OBTAINED BY TORTURE AND ILL-TREATMENT: PROCEDURES AND PRACTICES* <https://cti2024.org/wp-content/uploads/2021/01/CTI-Exclusionary_Rule_Tool_8-2020_FINAL_.pdf > accessed on August 25, 2024.

በሕግ ማስከበር ተግባራት ውስጥ የኃይል አጠቃቀም በዋናነት የሚተዳደረው በማንኛውም ጊዜና በሀገር ውስጥ ሕግ ውስጥ ተፈፃሚነት ባለው በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ነው፡፡ ምንም እንኳ የሕግ አስገዳጅነት ባይኖራቸውም እ.ኤ.አ. በ1979 የወጣው የተባበሩት *መንግሥታት* የሕግ አስከባሪ አካላት የ*ሥነ* ምግባር ደንብ እና እ.ኤ.አ. በ1990 በተባበሩት *መንግሥታት* ድርጅት ጉባኤ የጸደቁት የሕግ አስከባሪ አባላት የኃይልና የጦር *መሣሪያ* አጠቃቀም *መሠረታዊ* መርሆዎች በሕግ ማስከበር ተግባራት ውስጥ የኃይል አጠቃቀምን በተመለከተ ተጨማሪ *መመሪያ* ይሰጣሉ፡፡ በተለይ መርህ 8 “ከእነዚህ *መሠረታዊ* መርሆዎች ለማፈንገጥ የውስጥ የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ሌላ ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታና የመሳሰሉ ልዩ ሁኔታዎችን ምክንያት ለማድረግ አይቻልም” ይላል፡፡

የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት የመኖር መብትን ሳይጥስ ነገር ግን ሕይወትን ሊያሳጣ የሚችል የኃይል አጠቃቀም ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን በዝርዝር የሚጠቅስ ብቸኛው የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት ነው፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች በአንቀጽ 2 ላይ እንደተደነገጉት፡- (ሀ) ማንኛውም ሰው ከሕገወጥ ጥቃት ለመከላከል፤ (ለ) ሰዎችን በሕጋዊ መንገድ ለመያዝ /በቁጥጥር ስር ለማዋል/ ወይም በሕጋዊ መንገድ የታሰረ ሰው እንዳያመልጥ ለመከላከል፤ (ሐ) ሕዝባዊ አመጽ/ሁከትን ለማስቆም ሕጋዊ በሆነ መንገድ የተወሰደ የኃይል እርምጃ ናቸው፡፡

 DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.8

### 2.10.5 በማሰቃየት እና ሌሎች የኢሰብዊ አያያዝ ዓይነቶች መካከል ያለውን የልዩነት መስመር መወሰን አስቸጋሪ መሆኑ[76]

ማሰቃየት ፈጽሞ የተከለከለ ሲሆን ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ስያሜው እንደሚያመለክተው አንጻራዊ ጽንሰ ሐሳብ ነው::[77] ሕይወትን ለማዳን ሲባል ማሰቃየት እንደአስፈላጊ የመጨረሻ አማራጭ ተደርጎ ቢታሰብ እንኳ የሚፈጸምባቸው ልዩ ሁኔታዎችን በግልጽ መወሰን ያስፈልጋል:: ማሰቃየት የሚያበቃው እና 'መጠነኛ አካላዊ ጫና' ('*moderate physical pressure*') የሚጀምረው የት ነው? ለማሰቃየት ማስፈራራት የታሰበውን ውጤት ካላስገኘ ምን ይሆናል? ተጠርጣሪው ከባድ ስቃይ እንዲደርስበት ከተደረገ በኋላ አሁንም አስፈላጊውን መረጃ ካላቀረበ ምን ይሆናል/ይደረጋል? በምን ደረጃ ላይ ይቆማል? የተመጣጣኝነት መርሆ በተግባር ምን ይሆናል? 'ተገቢ' ማሰቃየት ወይም 'መጠነኛ አካላዊ ጫና' ተብሎ የሚጠራው ምንድን ነው? ማሰቃየት የሚያበቃው እና 'መጠነኛ አካላዊ ጫና' የሚጀምረው የት ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ያህል ከማሰቃየት ዓይነቶች መካከል ሕመም በሚያስከትል መልኩ እስረኞች ላይ አካላዊ ድብደባ መፈጸም፣ ሆን ብሎ በአከርካሪ

[76] Pau Pérez-Sales, 'Drawing the fine line between interrogation and torture: towards a Universal Protocol on Investigative Interviewing' [2017] 27/2 TORTURE <https://www.researchgate.net/publication/326655778_Drawing_the_fine_line_between_interrogation_and_torture_towards_a_Universal_Protocol_on_Investigative_Interviewing> accessed on August 28, 2024; Association for the Prevention of Torture, *The Definition of Torture Proceedings of an Expert Seminar* <https://www.apt.ch/sites/default/files/publications/Definition%20of%20Torture_Seminar_EN.pdf> accessed on August 29, 2024; *Is torture ever justified?* <https://www.google.com/url?sa=t&source=web&rct=j&opi=89978449&url=https://www.economist.com/international/2007/09/20/is-torture-ever-justified&ved=2ahUKEwis5OvZyt6IAxXYZ_EDHX4OOKoQFnoECCwQAQ&usg=AOvVaw0r0-aArS8xg5QdhupUn0gR>; Mary-Hunter Morris McDonnell, Loran F. Nordgren and George Loewenstein, 'Torture in the Eyes of the Beholder: The Psychological Difficulty of Defining Torture in Law and Policy' [2011] 44:87 Vanderbilt Journal of Transnational Law <https://www.cmu.edu/dietrich/sds/docs/loewenstein/TortureEyesBeholder.pdf> accessed on August 29, 2024; Christian M. De Vos, 'Mind the Gap: Purpose, Pain, and the Difference between Torture and Inhuman Treatment' [2007] 14/2 Human Rights Brief <https://digitalcommons.wcl.american.edu/hrbrief/vol14/iss2/2/> accessed on August 28, 2024.

[77] Nowak (n 1) 676.

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

አጥንት ላይ ጫና የሚፈጥር ወንበር መጠቀም ወይም እስረኞችን በተወሰኑ የሚያሰቃዩ አቀማመጦች እንዲቀመጡ ማስገድድ፣ ለእስረኞች ስለመብታቸው መዋሸት/ሐሰትን መናገር፣ በምግብ እጦት ወይም በረሃብ ምክንያት ማሰቃየት፣ ከተወሰኑ ሰዓታት ወይም ቀናት በላይ የሚቆይ ሆን ተብሎ እንቅልፍ ማሳጣት፣ ከፍተኛ ድምጽ ያለውን ሙዚቃ ያለማቋረጥ ማሰማት ወይም በጣም ከፍተኛ ሙቀት መጠቀም፣ የመስጠም ስሜትን ለማነሳሳት ውሃ በእስረኛው አፍና አፍንጫ ውስጥ በኃይል እንዲገባ የሚደረግበት የምርመራ ዘዴ፣ የኤሌክትሪክ ንዝረት፣ የእስረኞች ቤተሰብ አባላትን አስገድዶ ለመደፈርና ለማሰቃየት ዛቻ መፈጸም፣ የእስረኞች እጆችን ሕመም በሚያስከትል መልኩ ከወንበራቸው ጀርባ ማሰር፣ እርቃን ማስቀረት እና እስረኛው ላይ ምራቅ መትፋት ወይም ሌላ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ በዋናነት ይጠቀሳሉ። በአንጻሩ ደግሞ ላልተገለጸ ጊዜ ለብቻ ተገልሎ መታሰር ወይም እስረኛን በተለየ የእስር ክፍል ውስጥ ማቆየት፣ በወንጀል የተጠረጠሩ እስረኞች ቤተሰብ አባላትን ለመያዝ (በቁጥጥር ስር ለማዋል) ዛቻ መፈጸም፣ እስረኞች ከቦታ ወደ ቦታ ሲዘዋወሩ ወይም አንዳንዴም ለእስረኞቹ ጩኸት ወይም የስሜት መገንፈል የአጸፋ ምላሽ በሆነ መልኩ ዝቅተኛ ደረጃ በደል መፈጸም /እስረኞችን መምታት/፣ እስረኞችን ስለመብታቸው ለማሳሳት ዝቅተኛ-ደረጃ ማታለል መፈጸም፣ እስረኞችን ወደ ወንበራቸው ጎን በማይመች ሁኔታ ማሰር፣ እንቅልፍ ማጣት (የማያቋርጥ ምርመራ በሚመስል ግን ከተራዘሙ 'ዕረፍቶች' ጋር እየተቋረጠ ስልታዊ በሆነ መንገድ የተፈጸመ እንደሆነ)፣ ከተፈቀደው ዝቅተኛ መስፈርት በላይ የሆነ ምግብን ጨምሮ ማበረታቻዎችን መስጠትና መልሶ መውሰድ፤ ከድምፅ፣ ከሙቀት ወይም ከንጽህና ጋር የተያያዘ ለማይመች ግን የማያሳምም አካባቢ መጋለጥ፤ የማይመች ወንበር መጠቀም ወይም ሕመም ለመፍጠር ተብሎ የተደረገ ባይሆንም እስረኛው በማይመች አቀማመጥ እንዲቀመጥ ማድረግ፤ በአጠቃላይ እስከ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ድረስ ባይደርስም አንድ እስረኛ አቅም እንደሌለውና እንደቀለለ እንዲሰማው ማድረግ እንደ 'መጠነኛ አካላዊ ጫና' ይቆጠራሉ።

 DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.8

### 2.10.6 በሕይወት ከመኖር መብት ይልቅ ማሰቃየት መከልከሉ ፍፁም መሆኑ

በሕይወት የመኖር መብት እጅግ በጣም መሠረታዊው የሰብዓዊ መብት ነው፡፡ ነገር ግን ከማሰቃየት ወይም በባርነት ከመያዝ የመጠበቅ መብት በተቃራኒው የመኖር መብት ፍፁም መብት አይደለም፡፡ በተለይም የሞት ቅጣትን በሚፈቅዱ የሕግ ሥርዓቶች ውስጥ በሕይወት የመኖር መብት ፍፁም ነው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ሕግ (*international humanitarian law*) 'በሕጋዊ የጦርነት ድርጊት' ምክንያት የአንድ ተዋጊ ሞት የሕይወት መብት ጥሰት ተደርጎ አይቆጠርም፡፡ በተመሳሳይ የሕግ አስከባሪዎች አንድን ሰው ቢገድሉ (ወይም ሕይወት ቢያጠፉ) እና ሞቱ የተከሰተው ራስን ወይም ሌላ ሰውን ለመከላከልና ለመሳሰሉት ሕጋዊ ዓላማዎች ፍፁም አስፈላጊ በሆነ የኃይል አጠቃቀም ወይም በሕግ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት በተፈጸመ መያዝ ምክንያት ወይም በሕጋዊ መንገድ የታሰረ ሰው እንዳያመልጥ ለመከላከል ወይም ሕዝባዊ አመጽ/ሁከትን ለማስቆም በተወሰደ የኃይል እርምጃ እንደሆነ ድርጊቱ በሕይወት የመኖር መብትን ሊጥስ አይችልም፡፡ ስለሆነም ፖሊስ የሌሎች ሰዎችን ሕይወት ለመጠበቅ በወንጀለኛው የመኖር መብት ላይ ጣልቃ መግባት ይችላል፡፡ ፖሊስ ሰዎቹን በቅርብ ከሚደርስ ከባድ ከሆነ አደጋ ለማዳን ሲሞክር እንደ የመጨረሻ አማራጭ በወንጀል አድራጊው ላይ እንዲተኩስ ይፈቀድለታል፡፡ ምክንያቱም በወንጀል አድራጊው እና በተጎጂው መካከል ቀጥተኛ የማስተዋል/የስሜት ግንኙነት የለም፡፡ ተጠርጣሪው በትክክል ወንጀለኛው ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ ነገር ግን አንድ ከባድ ውንብድና ወይም ዘረፋ የሚፈጽም ሰው በግልጽና በቀጥታ የሌሎችን ሕይወት አደጋ ላይ ይጥላል፡፡[78]

[78] F. Jessberger, 'Bad Torture – Good Torture?' [(2005] 3/5 Journal of International Criminal Justice <https://academic.oup.com/jicj/article-abstract/3/5/1059/2188899?redirectedFrom=fulltext> accessed on August 26, 2024.

#### 2.10.7 ማሰቃየት የሥራ መግለጫ ቢሆን እንኳ አፀያፊና መልሶ የሚያሰቃይ ሥራ መሆኑ

ማሰቃየትን እንደተገቢ የምርመራ ዘዴ መተግበር ማለት ልዩ ሁኔታ ቢሆን እንኳ የአንድ የፖሊስ አባል (ወይም በፖሊስ ተቋም ውስጥ የአንዳንድ ልዩ ክፍሎች) ሥራ አካል መሆን አለበት የሚል አንደምታ አለው:: ይህም ማለት የፖሊስ አባላት ተግባራት በተለዩ ሁኔታዎች ውስጥ ማሰቃየት መፈጸምን ያካትታሉ:: ሆኖም በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ማሰቃየት የሚፈጽሙ ሰዎች የሥነ ልቦና ጉዳት ይደርስባቸዋል::[79] ከጅምሩ የሰው ልጅ በሌሎች መሰሎቹ ላይ ከሚፈጽማቸው እጅጉን አሰቃቂና አረመኔያዊ ድርጊቶች መካከል አንዱ ማሰቃየት እንደመሆኑ መጠን ማሰቃየት የሚፈጽሙ ሰዎች የአዕምሮ ሰላም አይኖራቸውም::[80] አይደለም ዘግናኙን የማሰቃየት ተግባር መፈጸም ይቅርና የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች እንኳ በሥራቸው ምክንያት ያጋጠማቸውን ጭንቀት መቋቋም አቅቷቸው ራሳቸውን ያጠፉበት አጋጣሚዎች እንደነበሩ መረጃዎች ያሳያሉ::[81] በመሰረቱ ሁሉም መርማሪ የፖሊስ አባላት ሙያዊ ሥነ ምግባርን በተከተለ አኳኋን ነፃና ገለልተኛ ሆነው ተግባራቸውን ሊያከናውኑ ይገባል::

#### 2.10.8 የማሰቃየት ልምድ በእንጭጩ ካልተገራ ልጓም የሌለው ፈረስ መሆኑ

ማሰቃየትን እንደምርመራ ዘዴ መጠቀም ወይም ማሰቃየት ተፈጽሞ ሲገኝ በመንግሥት በቸልታ ከታለፈ በፍጥነት ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን ይችላል::[82] ማሰቃየት የሚጀምረው በተለዩ ሁኔታዎች ብቻ እንደሚያገለግል ዘዴ ቢሆንም

[79] Michael Davis, 'Torturing Professions' [2008] International Journal of Applied Philosophy <https://www.google.com/url?sa=t&source=web&rct=j&opi=89978449&url=https://www.researchgate.net/publication/314450621_Torturing_Professions&ved=2ahUKEwiQq__33uCIAxWbR_EDHUStALkQFnoECBEQAQ&usg=AOvVaw3Jr_034Dv-0WKzPcoP_aCs> accessed on August 28, 2024.

[80] US Department of Veteran Affairs, *Journalists and PTSD* <https://www.ptsd.va.gov/professional/treat/care/journalists_ptsd.asp> accessed on August 28, 2024;

[81] *How Photographer Kevin Carter's Work During The Sudan Famine Drove Him To Suicide* <https://allthatsinteresting.com/kevin-carter%20%20> accessed on August 28, 2024; Felix Adeoye, *Learn From A Man Who Murdered Himself* <https://medium.com/writers-blokke/lessons-from-kevin-carter-death-42cfb9179019> accessed on August 28, 2024.

[82] Massimo La Torre, *Reopening Pandora's Box: The Return of Torture (and of Moral Monstrosity)* <https://www.researchgate.net/publication/330313120_Reopening_Pandora's_Box_The_Return_of_Torture_and_of_Moral_Monstrosity> accessed on August 20, 2024.

የመስፋፋት እና ወደ አጠቃላይ ልምድነት የማደግ አደጋ አለው:: ማሰቃየትን በየትኛውም ስም (ለምሳሌ ‘መጠነኛ አካላዊ ጫና’ ብሎ መጠሪያ መስጠት) ተቋማዊ ማድረግ በሕግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የተገነባባቸው እጅግ መሠረታዊ መርሆዎችን ዋጋ የሚያሳጣ አንሸራታች ቁልቁለት መሆኑ አሌ የማይባል ሀቅ ነው:: እንደማሳያ በእስራኤል ሀገር በፍርድ ቤት ውሳኔ በወንጀል ምርመራ ወቅት ማናቸውንም ዓይነት አካላዊ ኃይል መጠቀም ሙሉ በሙሉ የታገደበት አጋጣሚም አለ:: እ.ኤ.አ. በ1987 እስራኤል በዓለም ላይ ማሰቃየት ሕጋዊ የሆነበት ብቸኛ ሀገር የነበረች[83] ቢሆንም እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 6 ቀን 1999 (ጳጉሜ 1 ቀን 1991 ዓ.ም.) ፐብሊክ ኮሚቲ አጌንስት ቶርቸር ኢን ኢዝራኤል (*PCATI*) በተባለ መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት እና በእስራኤል መንግሥት ጉዳይ የእስራኤል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሀገሪቱ የደኅንነት ኤጀንሲ (ወይም ’*Shin Bet* በመባል የሚታወቀው በእስራኤል ደህንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የተጠረጠሩ ሰዎችን የመመርመር ኃላፊነት የተሰጠው የደኅንነት ፖሊስ) የሚጠቀማቸው በርካታ አካላዊ የምርመራ ዘዴዎች በወቅቱ በነበረው የእስራኤል ሕግ መሠረት ሕገወጥ እንደሆኑ በአንድ ድምፅ ወስኖ ነበር::[84]

---

[83] OMCT, *It’s now (even more) official: torture is legal in Israel* <https://www.omct.org/en/resources/blog/its-now-even-more-official-torture-is-legal-in-israel> accessed on August 30, 2024.

[84] H.C. 5100/94, Pub. Comm. Against Torture in Israel v. The State of Israel et al.; Matthew G. Amand St., ‘Public Committee against Torture in Israel v. The State of Israel et al: Landmark Human Rights Decision by the Israeli High Court of Justice or Status Quo Maintained’ 25/3 North Carolina Journal of International Law, 1999.

## 3. መደምደሚያ

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ማሰቃየትም ሆነ ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ኢሰብዓዊ የሆኑና ክብርን የሚያዋርዱ አያያዞችና ቅጣቶች ሁልጊዜም የተከለከሉ ናቸው። እነዚህ ድርጊቶች ሕገወጥ መሆናቸው ከስድስት አስርተ ዓመታት በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደንግጓል። በአሁን ጊዜ 174 ሀገራት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንን እና የፀረ ማሰቃየት ስምምነትን ተቀብለው አጽድቀዋል። ዓለም አቀፍና አኅጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችን ማጽደቅ አንድ ወሳኝ እርምጃ ቢሆንም ማጽደቅን ተከትሎ ወደ ውጤታማ ትግበራ የሚያመሩ ተጨባጭ ማሻሻያዎች ያስፈልጋሉ። የፀረ ማሰቃየት ስምምነትን ያጸደቁ ሀገራት ማሰቃየትን ለማስወገድ የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። በተለይም የፀረ ማሰቃየት ስምምነት አባል ሀገራት በሥልጣናቸው ስር ባለ ማንኛውም ግዛት ውስጥ የሚፈጸም ማሰቃየትን ለመከላከል ውጤታማ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያስገድዳል። ማሰቃየት ፍፁም መከልከሉ ሕልምና ምኞት ወይም 'ላም አለኝ በሰማይ ወተትዋንም አላይ' ሳይሆን በመርህ ደረጃም ሆነ በተግባር ተጨባጭ ተስፋ መሆን አለበት።

በሁሉም ሁኔታዎች ሌላው ቀርቶ የሽብር ድርጊቶች ወይም የተደራጁ ወንጀሎችን በመሳሰሉ በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች እንኳ ማሰቃየት ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። በሰላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ (ወይም በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ) ለሀገርና ለሕዝብ ሰላምና ደኅንነት ከፍተኛ ስጋት የሆኑ ወንጀሎች (ለምሳሌ ከፍተኛ የሀገር ክህደት ወይም ከፍ ያለ ክዳት፣ የጦር ወንጀል፣ የሰው ዘር ማጥፋት፣ ከባድ የሰው ግድያ፣ ከባድ ውንብድና፣ የሽብር ወንጀል፣ ወዘተ) እንኳ ቢፈጸሙ ማሰቃየት ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። ብሔራዊ ደኅንነትን ለመጠበቅ እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል ማሰቃየት ተገቢ ነው የሚለው የተለመደ መከራከሪያ ውሃ አይቋጥርም።

ይሁን እንጂ በዓለም ዙሪያ ያሉ መንግሥታት ሰዎችን በማሰቃየት ያሉትን ጥቂት የሕግ ጥበቃዎችን መጣስ ቀጥለዋል። መንግሥታት ማሰቃየትን ለተለያየ ምክንያት ይጠቀማሉ፤ በዋናነት መረጃን ለማግኘት፣ ሰላማዊ ተቃውሞን ለማፈን ወይም ጭካኔ የተሞላበት ቅጣት ሆኖ ያገለግላል። ብዙውን ጊዜ ማሰቃየት ወንጀሎችን

**ለመመርመር መደበኛው ዘዴ ነው። ብዙ ሀገራት ማሰቃየት የተለየ ወንጀል መሆኑን በብሔራዊ ሕጎቻቸው ውስጥ በግልጽ መደንገግ አልቻሉም። ማሰቃየትን ማስወገድ ያለመው የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ከተካሄደ ከአምስት አስርተ ዓመታት በኋላ አሁንም ሰዎች ማሰቃየት ይደርስባቸዋል። የሀገርን ሰላምና ደኅንነት የማስከበርና የወንጀል ምርመራ ሥራ በሕግ አግባብ ብቻ ሊሆን ይገባል። ማሰቃየት በመጀመሪያ ደረጃ እንዳይፈጸም ለመከላከል አሁንም ብዙ የውትወታ ሥራ ይቀራል። ማሰቃየትን ሁልጊዜ 'አይ' ማለት አለብን።**

## Conflict of Interest

The author declares no conflict of interest.

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl